የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
AMHARA REGION SUPREME COURT

# የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ አጭር ማብራሪያ

ሰኔ 2017

ባሕር ዳር

## ማውጫ


1. **መግቢያ** ........ 1
2. **ደንቡን ማውጣት ለምን አስፈለገ?** ........ 2

   2.1. ደንቡ እንዴት ተዘጋጀ? ........ 7

   2.2. በደንቡ ላይ ውይይት ስለመደረጉና ግብዓቶች የተሰበሰቡበት ስለመሆኑ ........ 8
3. **የደንቡ ዓላማዎች** ........ 8
4. **በደንቡ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች** ........ 11

   4.1. የደንቡ የተፈጻሚነት ወሰን ........ 11

   4.2. የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል መርሕ ........ 13

   4.3. ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ስለሆኑ ሰዎችና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይከፈልባቸው ክሶች ........ 13

   4.4. የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ስለሚከፈልበት ጊዜ እና የአከፋፈል ሥርዓት ........ 18

   4.5. በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች እና በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠንና የሥሌት ዘዴ ........ 19

   4.6. ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ........ 25

   4.7. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ........ 26
5. **ማጠቃለያ** ........ 28

# 1. መግቢያ

የአማራ ክልል ምክር ቤት ከየካቲት 4-7/2017 ዓ.ም ባካሄደው 6ኛ ዙር፤4ኛ ዓመት፤9ኛ መደበኛ ጉባኤ መርምሮ ከአጸደቃቸው ሕጎች መካከል አንዱ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ ቁጥር 297/2017 ዓ/ም[1] መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ አዋጅ ከአካተታቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል ደግሞ በአንቀጽ 12 ስር የተመለከተው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን የሚመለከተው ይገኝበታል፡፡ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) ስር "ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ባከበረ መልኩ ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት ክፍያ ከሚመለከታቸው ባለጉዳዮች ይሰበስባሉ" በሚል የተደነገገ ሲሆን በንዑስ (2) ስር ደግሞ " የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን፣ ስሌት እና ተያያዥ ጉዳዮች በምክር ቤቱ በሚወጣ ደንብ" እንደሚወሰን ተመልክቷል፡፡

በዚህ አግባብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የሚያስችል ረቂቅ ደንብ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኩል ለክልሉ ምክር ቤት በተመሳሳይ ጊዜ ቀርቦ ስለነበር የክልሉ ምክር ቤት እንደዚሁ ረቂቁን በዝርዝር ተመልክቶ የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን መወሰኛ ደንብ ቁጥር 17/2017 ዓ/ም አጽድቋል፡፡ ይህም በክልሉ ዝክረ-ሕግ 30ኛ ዓመት፣ቁጥር 26 ሚያዝያ 11 ቀን 2017 ዓ/ም ታትሞ ወጥቷል፡፡ የደንቡ አንቀጽ 28 ይህ አዲስ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ በዝክረ-ሕግ ታትሞ ከወጣበት ሚያዝያ 11 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል በግልጽ ይደነግጋል፡፡

በዚህም መሠረት በአሁኑ ወቅት ይህ ደንብ በክልሉ ሁሉም ፍርድ ቤቶች እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ደንቡ በርካታ አዳዲስ ነገሮችን የያዘ በመሆኑ የተሟላ ትግበራ እና ተመሳሳይ አፈጻጸም እንዲኖር የሚያግዝ ጽሑፍ ማዘጋጀት አስፈላጊነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ በተጨባጭም በየአካባቢው ያሉ ፍርድ ቤቶች በትግበራ ወቅት ችግር ገጠመን በማለት አንዳንድ ጥያቄዎችን እያቀረቡ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ አጭር ማብራሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

ማብራሪያው በቅድሚያ ደንቡን ማውጣት ለምን እንደአስፈለገ በክፍል 2 ሥር ምጥን ማብራሪያ ያቀርባል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ደንቡ እንዴት እንደተዘጋጀ፣ በዝግጅት ሂደቱ ላይ በማገናዘቢያነት ጥቅም ላይ የዋሉ እንዲሁም በውይይት ላይ ስለተሳተፉና ግብአት ስለሰጡ አካላት በወፍ በረር መረጃ ይሰጣል፡፡ በማስከተልም ጽሑፉ በክፍል 3 ሥር የደንቡን ዋና ዋና ዓላማዎች ያቀርባል፡፡

ክፍል 4 ደግሞ በደንቡ ውስጥ በተካተቱ አንኳር ጉዳዮች ላይ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ ይኸውም ስለደንቡ የተፈጻሚነት ወሰን፣ ስለየዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የመክፈል መርሕ፣ ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ስለሆኑ ሰዎች እና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ስለማይከፈልባቸው ክሶች፣ በደሃ ደንብ መሠረት በነጻ ስለሚደረግ ክርክር እና በክርክር መጨረሻ ስለሚኖር የክፍያ ሁኔታ፣ የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ስለሚከፈልበት ጊዜ እና የአከፋፈል ሥርዓት፣ በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች እና በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠንና የሥሌት ዘዴን በተመለከተ፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈል ክፍያ እና የክፍያ መጠን እንዲሁም ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ገለጻ ያቀርባል፡፡ ከዚህ በማስከተል ደግሞ በመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች ውስጥ ስለተካተቱ ቁም-ነገሮች ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያ ያቀርባል፡፡

---

[1] በዝክረ-ሕግ 29ኛ ዓመት፣ቁጥር 25 ሚያዝያ 4 ቀን 2017 ዓ/ም ታትሞ የወጣና ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ፡፡

## 2. ደንቡን ማውጣት ለምን አስፈለገ?

ስለአዲሱ የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን መወሰኛ ደንብ ቁጥር 17/2017 ከመነጋገራችን በፊት ይህ ደንብ እስኪወጣ ድረስ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ሲሠሩበት ስለነበረው ሕግ እና ስለሕጋዊ መሠረቱ ማውሳት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያም የክልሉ ሕግ አውጭ ምክር ቤት ይህን አዲሱን ደንብ ለማውጣት ያስቻለውን ሕጋዊ መሠረት ማየት ያስፈልጋል፡፡

ለመሆኑ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት ሲመጣ የነበረውን ተከራካሪ ወገን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሲያስከፍሉ የቆዩት በምን ሕግ መሠረት ነበር? በተግባር እንደሚታወቀው በክልሉ ውስጥ ሲሠራበት የቆየው ቀደም ሲል በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ወጥቶ የነበረ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 ነው፡፡ ይህ ከ72 አመት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረ አሮጌ ሕግ እንደሆነ ዘመኑ ብቻ ይናገራል፡፡ ይህ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ እንዴት ብሎ በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚ ሊሆን እንደቻለ የሕግ መሠረቱን መመርመር ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ ከሦሥት አሥርት አመታት በፊት አሁን "አማራ ክልል" እየተባለ በሚጠራው ክልል ውስጥ ራሱን የቻለ የዳኝነት አካል ሲቋቋም ፍርድ ቤቶቹ እንዲሠሩባቸው የተደነገጉ መሠረታዊ እና የሥነ- ሥርዓት ሕጎች ምን እንደነበሩና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የነበረውን የሕግ መሠረትና አሠራር መፈተሽ ይጠይቃል፡፡ ይሁን እንጅ አሁን ከያዝነው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው በአጭሩ ማውሳት ብቻ በቂ ነው፡፡

አሁን የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት እየተባለ የሚጠራው ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር (ኢሕአዴግ) መሪነት በተቋቋመው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት[2] ወቅት በወጣው የብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 3 (1) ሥር እንዲቋቋም የተደረገ መሆኑ ይታወሳል፡፡ ይህን ተከትሎ የክልል ሦሥት የሽግግር መስተዳድር የሚባል በአሁኑ የአማራ ክልል የተቋቋመና የክልል ሦሥት የሽግግር መስተዳድር ሕገ-መንግሥት[3] መታወጁም የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 21 ሥር ሦሥት የክልሉ የሽግግር መስተዳድር አካላትን ማለትም ሕግ አውጭ፣ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካላት እንደሚዋቀሩ የደነገገ ስለነበርና የሽግግር መስተዳድሩ ሕግ አውጭ አካል በክልሉ ውስጥ የዳኝነት አካላትን እንደሚያቋቁም በአንቀጽ 27 (10) ሥር ስለተደነገገ ይህን ተከትሎ የክልሉ የሽግግር መስተዳድር ክልል ምክር ቤት (ሕግ አውጭ) የክልሉን ሦሥት እርከን ፍርድ ቤቶች ማለትም የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና የወረዳ ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 3/1985 አንቀጽ 4 ሥር አቋሚል፡፡[4] ይኸው አዋጅ የክልሉ ፍርድ ቤቶችን ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣንና በማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት ሥልጣን ሥር የሚወድቁትን በውክልና የመዳኘት ሥልጣን በግልጽ ከደነገገ በኋላ ፍርድ ቤቶቹ የሀገሪቱን መሠረታዊ እና የሥነ-ሥርዓት ሕጎች በመቀበል (incorporation or reception of the substantive and procedural laws of the country as laws to be applied within the Region) እንዲሠሩባቸው ያደረገ ነበር፡፡ ከዚያ ወዲህ የወጡ ሕጎችም በተመሳሳይ መንገድ እየተቀበሉ ነው የቀጠሉት፡፡ በቅርብ ጊዜ የወጣው የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 281/ 2014 አንቀጽ 26 እና 27 እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥለዋል፡፡ ስለሆነም ቀደም

---

[2] የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ከሐምሌ 15 ቀን 1983 እስከ ነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ/ም የቆዩ መሆኑን ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ/ም በነጋሪት ጋዜጣ፣ 50ኛ አመት፣ቁጥር 1 ታትሞ ከወጣው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር እና ነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ/ም በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣1ኛ አመት ቁጥር 1 ታትሞ ሥራ ላይ ከዋለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987 በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

[3] ይህ በክልሉ የሕግ-ልሣን /ሕግ ማሳወቂያ ጋዜጣ/ ዝክረ-ሕግ አዋጅ 2/1985 የወጣ ነበር፡፡

[4] ይህ በዝክረ-ሕግ ሰኔ 18 ቀን 1985 ዓ/ም ታትሞ የወጣው አዋጅ ስያሜው "የክልል ሦሥት የሽግግር መስተዳድር ፍርድ ቤቶችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 3/1985" የሚል ነበር፡፡

ሲል የተጠቀሰው የዳኝነት አገልግሎት ማስከፈያ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 177/1945 በዚህ መሠረት ሲሠራበት እንደቆየ መረዳት ይቻላል፡፡

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 52 (1) ለፌዴራሉ መንግሥት ለብቻ ወይም ለፌዴራል መንግሥትና ለክልል መንግሥታት በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል መንግሥታት ሥልጣን ስር እንደሚወድቅ ይደነግጋል፡፡ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን አስመልክቶ ለፌዴራሉ መንግሥት ለብቻው ሆነ የፌዴራል መንግሥት ከክልል መንግሥታት ጋር በጋራ ሕግ እንዲያወጡ በግልጽ ያልተሰጠ መሆኑን የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 97 እና 98 ከሚደነግገው መረዳት ይቻላል፡፡[5] ከዚህ አንጻር በፌዴሬሽኑ ውስጥ የታቀፉ የክልል መንግሥታት የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን አስመልክቶ ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም መሠረት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ ቁጥር 8/2016ን  በክልሉ የሕግ ማውጫ ጋዜጣ (መገለተ ኦሮሚያ) ከየካቲት 11 ቀን 2016 ጀምሮ በማወጣት ተፈጻሚ አድርጓል፡፡ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤትም ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ክፍ ሲል እንደተገለጸው ከየካቲት 4-7/2017 ዓ.ም ባካሄደው 6ኛ ዙር፤4ኛ ዓመት፤9ኛ መደበኛ ጉባኤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያን መወሰኛ ደንብ ቁጥር 17/2017 ዓ/ም አጽድቋል፡፡ ይህም በክልሉ ዝክረ-ሕግ 30ኛ ዓመት፣ቁጥር 26 ሚያዝያ 11 ቀን 2017 ዓ/ም ታትሞ ወጥቷል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ቀድሞ የነበረውን ሕግ በመተው ይህን አዲስ ደንብ እንዲያወጣ ያደረጉት ምክንያቶች በርካታ ናቸው፡፡ ከዋና ዋና ምክንያቶቹ መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሱት በደንቡ መግቢያ ላይ የተመለከቱት ናቸው፡፡ ይኸውም ከ72 ዓመታት በላይ በቆየው ሕግ በርካታ ያልተሸፈኑ ነገሮች መኖራቸው የመጀመሪያው ምክንያት ነው፡፡ የሕግ ማስታወቂያው በወጣበት ዘመን የማይታወቁና በሂደት ወደፍርድ ቤት እየቀረቡ ዳኝነት የሚጠየቅባቸውና የዳኝነት አገልግሎት ሊከፈልባቸው የሚገቡ በርካታ አዳዲስ ጉዳዮች ተፈጥረዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ፡

- አቤቱታ ለማሻሻል የሚቀርብ አቤቱታ፣
- አንድ በአስተዳደራዊ አካል ውሳኔ ያገኘን ጉዳይ በክለሳ ወይም በይግባኝ ለማሳረም የሚቀርብ አቤቱታ፣
- የተሰጠ ብይን ወይም ትዕዛዝ ለማስነሳት የሚቀርብ አቤቱታ፣
- የመዝገብ ይጣመርልኝ አቤቱታ፣
- በክርክር ላይ ባለ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት የሚቀርብ አቤቱታ፣
- ዳኝነት እንደገና እንዲታይ (Review of judgement) በሚል የሚቀርብ አቤቱታ፣
- የተዘጋ መዝገብ እንደገና ለማንቀሳቀስ የሚቀርብ አቤቱታ፣
- የተሰጠ እግድ ለማስነሳት የሚቀርብ አቤቱታ፤... ወዘተ

የመሳሰሉት ከዚህ ቀደም የዳኝነት የማይከፈልባቸው (legal gaps) ነበሩ፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህና የመሳሰሉት የፍርድ ቤትንና የተቃራኒ ወገን ተከራካሪን ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት የሚወስዱ መሆናቸው በተግባር የታዬና የሚታወቅ ነው፡፡ ምንም የዳኝነት አገልግሎት ስለማይጠየቅበትም እንዲሁ ያለበቂ ምክንያትም ቢሆን አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ትዕዛዝ ወይም ብይን ለመጠባበቅ በር የከፈተ ነበር፡፡ ከጊዜ፣ ጉልበትና ወጭ አልፎ ያለአግባብ ክርክርን ወደኋላ ለመመለስ፣ ክርክርን ሆን ብሎ ሌላውን ወገን ለማድከም፣ ለማሰላቸትና ለማበሳጨት የሚውልባቸው አጋጣሚዎችም በልምድ ታይተዋል፡፡ የነበረውን ሕግ ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ይህ አንድ መነሻ ምክንያት ተደርጎ መወሰዱ ከዚህ አንጻር ተገቢነት ያለው ነው፡፡

[5] የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 99 የሚደነግገው እንደተጠበቀ ነው፡፡ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመንግሥት ከሚከፈል ግብር እና ታክስ ውጭ የሆነ ነገር ግን የመንግሥት የገቢ ምንጭ (non-tax revenue) ውስጥ የሚመደብ ለአገልግሎት የሚከፈል ክፍያ (fee) ዓይነት መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከ70 ዓመታት በፊት ለዳኝነት አገልግሎት ተብሎ የተቀመጠው ገንዘብ በአሁኑ ወቅት ካለው የገንዘብ የመግዛት አቅም (purchasing power of Birr) አንጻር ትርጉም አልባ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ በተለይ ለመጥሪያ እና ለመሳሰሉት የሚከፈል 0.50 ሣ (አምሣ ሣንቲም) ደረሰኙ (ወረቀቱ) ከሚጻፍበት በላይ ዋጋ እየወሰደ እንደነበር ሁሉም አገልግሎቱን ሲያገኝ የነበረ ሰው የሚመሰክረው ሐቅ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለውና ቀደም ሲል የነበረው የሀገሪቱ ገንዘብ የመግዛት አቅም በጣም ልዩነት የሚታይበት ከመሆኑ አንጻር በፍርድ ቤት ፊት የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች ሲከፍሉት የነበረውን መጠን ከወቅቱ አንጻር የማሻሻል አስፈላጊነት ግልጽና የማያከራክር ነው፡፡

የቆየውን ሕግ ለመለወጥ እንደምክንያት ከተጠቀሱት ምክንያቶች ሌላው በክልሉ ውስጥ የሚታዬውና በየጊዜው እየጨመረ የመጣው በትንሹም በትልቁም ጉዳይ የመካሰስ፣ የመከራከር ልምምድና አስፈሪ ዝንባሌ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከሚታወቀው በባሰና በተራዘመ ሁኔታ ሁሉን ነገር ያለበቂ አሳማኝ ሕጋዊ መሠረት ሁሉ ወደፍርድ ቤቶች ማቅረብና እስከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና ከዚያም አልፎ እስከፌዴሬሽን ምክር ቤት አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት በክርክር መሳሳብ (high litigiousness) ይታያል፡፡ ይህ በተከራካሪዎች በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ከሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ፣ስነ-ልቦናዊ እና ሌላም ጫና በአሻገር እየበዛ በሄደ ቁጥር በአጠቃላይ በኅብረተሰቡና በሀገር ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል ይሆናል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በስፋት ሲነገር እንደሚሰማውና አንዳንድ በፍርድ ቤቶች ፊት የሚደረጉ ክርክሮች እንደሚያመላክቱት ከቅን ልቦና ውጭ ሌላውን ወገን በክርክር ለማድከም ወይም ፍርድ ቤትን መጠቀሚያ በማድረግ ሌላውን ለማጥቃት እንዲሁም ከሌላ ወገን ጋር በሚኖር ሕጋዊ መስተጋብር ምክንያት የሚመጣን ግዴታ እና ኃላፊነት በወቅቱ ላለመወጣት ሲባል በስሌት/በተንኮል አቤቱታ በፍርድ ቤት በማቅረብ ጉዳዩ ከታለመለት ውጭ እንዲጓተት ፍርድ ቤትን እንደጊዜ መግዣ መጠቀም አለ፡፡ ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ሊያልቁ የሚችሉ ጉዳዮች ሳይቀር ፍርድ ቤት እንደሚቀርቡ እንዲሁም በቂ የክስ ምክንያት ሳይኖር ወይም ደግሞ ከቅን ልቦና ውጭ ሌላውን ሰው ለማጉላላት ሆን ተብሎ የሚቀርቡ ክሶች እንዳሉ ጠቋሚ ነገሮች አሉ፡፡ የክስ ምክንያት የሌላቸው፣ከፍርድ ቤት ውጭ ማለቅ የሚችሉ እንዲሁም ከቅን ልቦና ውጭ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን መቆጣጠር ወይም መግታት ተገቢ ነው፡፡ መንግሥት የዳኝነት አገልግሎት ከሚጠይቁ ሰዎች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚጠይቅበት አንዱ አሳማኝ ምክንያት እንዲህ ዓይነት በቂ የክስ ምክንያት የሌላቸውን፣ ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለማጉላላት ሲሉ ከቅን ልቦና ውጭ ክስ የሚያቀርቡትን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ (deterring frivolous litigation) ነው፡፡[6]

የአማራ ክልል ኅብረተሰብ እንደሌላው አካባቢ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ሁሉ ከጥንት ጀምሮ አለመግባባትን ከፍርድ ቤት ውጭ የሚፈታባቸው ልዩ ልዩ ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ ያለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች የነበሩትና አሁን ድረስ ያሉት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ የነበረው በጎ አሠራር እየተቀዛቀዘ መምጣቱና በእነዚህ ዘዴዎች መጠቀምን ትቶ ሁሉንም ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤቶች ይዞ የመቅረብ ልምምድ ሊያሳስብ የሚገባ ጉዳይ እየሆነ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አብዛኛውን ጊዜ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች የአንዱ ወገን አሸናፊ የሌላው ወገን ተሸናፊ ሆኖ የሚወጣበት ነው፡፡ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ፍርድና ውሳኔ እንደባህላዊ እና ኃይማኖታዊ የአለመግባባት መፍቻ ዘዴዎች አንተም- ተው፣አንተም ተው፣ በዚህ ብትጎዳ፣ በዚያ ትካሣለህ፣ ይቅር ለእግዚአብሔ/ለፈጣር መባባሉ ይሻላል፣… ወዘተ ተብሎ የሚቋጭ ባለመሆኑ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን

[6] See Rafael Mery Nieto, infra note 11. It has been noted (at P 110) "…. a free cost judicial system encourages levels of litigation socially inappropriate, because people do not take into consideration all the costs involved in a litigation process when deciding to bring suit. When costs are underestimated, because they only consider private costs, the result is that people litigate more."

ለቂምና ለማይሽር ቅራኔ የሚዳርግ ነው፡፡[7] የክልሉ ኅብረተሰብ የቆዩትንና ጠቃሚነታቸው የማያከራክሩትን (ከጎጅ ባህሎች እና ባዕድ አምልኮ ውጭ የሆኑ) ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች እንዲጠቀምባቸው ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ እንደእርቅ እና የሽምግልና ሥርዓት ካሉት የባህላዊ እና የኃይማኖታዊ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች በተጨማሪም ሌሎች ዘመናዊ አማራጭ የአለመግባባትና የጭቅጭቅ መፍቻ ዘዴዎችን መጠቀምም ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ የተሻለ ቤተሰባዊ፣ቤተዘመዳዊ፣ቡድናዊ እና አጠቃላይ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚዊ መስተጋብር እንዲዳብር ማድረግና የፍትሕ መስጫ መድረኩን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ውጭም እንዲዘወተር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች በቂ የክስ ምክንያት ቢኖራቸው እንኳ አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት (encouraging the resort to Alternative dispute resolution mechanisms) ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡[8] አዲስ የዳኝነት አገልግሎት ደንብ ማውጣት ያስፈለገበት አንዱ አሳማኝ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት የፍርድ ቤቶች የጉዳይ ብዛት/ክምችት ነው፡፡ በሌሎች ሀገሮች እንደሚደረገው ሁሉ የፍርድ ቤት የጉዳይ ብዛት ክምችትን መቀነሻ አንዱ መንገድ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሥርዓቱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ሆነ በዚህ በአማራ ክልል በየአመቱ ወደፍርድ ቤቶች የሚመጣው ጉዳይ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው፡፡ በፌዴራል መንግሥት ሆነ በየክልል መንግሥታት በየአመቱ የዳኛ ቁጥር ቢጨመርም አሁንም የጉዳዮች ክምችት ይታያል፡፡ የፍርድ ቤቶች የመረጃ ቋት እንደሚረጋግጠው በአማራ ክልል ውስጥ ከፍ ያለ የጉዳይ ክምችት አለ፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ የተፋጠነ ፍትሕ የመስጠት አቅምን ይቀንሳል፡፡ የፍርድ ጥራትንም ይቀንሳል፡፡ የጉዳይ ብዛት ክምችትን በመቀነስ (reducing court congestion)፣ የግድ ፍርድ ቤት መቅረብ ባለባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግና የተፋጠነ (efficient) እና ጥራት ያለው (quality) ፍትሕ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ እስከቅርብ ጊዜ ሲሠራበት የቆዬውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሥርዓት በአዲስ የክፍያ ሥርዓት መተካት ያስፈለገበት አንዱ ምክንያትም ይህ ነው፡፡

ሌላው መጠቀስ ያለበት ምክንያት ከፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት የሚያገኙ ሰዎች ከሌላው ግብር ከፋይ እና ማንኛውም ሰው በተለዬ አገልግሎት እያገኙ በመሆኑ በተወሰነ መጠን ለሚያገኙት አገልግሎት ክፍያ በመክፈል የመንግሥትን ጫና መቅረፍ የሚጠበቅባቸው መሆኑ ነው፡፡ የሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደሚያሳዬው የዳኝነት አካሉ የመንግሥት ተቋም ቢሆንም ለሚሰጠው የዳኝነት አገልግሎት የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት በማይጋፋ መልኩ ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የመንግሥትን ሸክም በመጠኑም ቢሆን ተገልጋዩ ኅብረተሰብ እንዲጋራ (funding the administration of justice) ይደረጋል፡፡ በእርግጥ በብዙ ሀገሮች የሚታዬው በዚህ መልክ የሚከፈለው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በቀጥታ የሚውለው ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከርና የዳኝነት አገልግሎቱን ለማስፋትና ለማዘመን ነው፡፡ ይህን በማድረግ አጠቃላይ የዳኝነት አገልግሎቱ የበለጠ ተደራሽ፣ግልጽ፣ቀልጣፋ፣ዘመናዊ፣ጥራት ያለው እና ውጤታማ እንዲሆን የማስቻል ልምድ ነው የሚታየው፡፡ መንግሥት ለፍርድ ቤቶች የሚመድበው በጀት ከታክስና ግብር በሚገኝ ብቻ ከሚወሰንና የዳኝነት አካሉ አቅም ከዚሁ አንጻር በጣም የተወሰነ ከሚሆን ይልቅ ከእንደዚህ ዓይነት አገልግሎቶች በሚገኝ ገቢ ተደጉሞ የበለጠ ቢጠናከር ተመራጭ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በቀጥታ ፍርድ ቤቶች እንዲጠቀሙ የተፈቀደ ባይሆንም የክልሉ መንግሥት በዚህ በኩል የሚሰበሰበውን ገቢ ታሳቢ በማድረግ የፍርድ ቤቶችን በጀት የበለጠ በማሳደግ ፍርድ ቤቶች የበለጠ ተደራሽ፣ ዘመናዊና

---

[7] See Pia Letto-Vanamo, "Access to Justice- A Conceptual and Practical Analysis with Implications for Justice Reforms", *2 (1) IDLO (International Development Law Organization) Voices of Development Jurists Paper Series (2005)*, P.4 (noting that "a court will normally be able to determine who is right and who is wrong according to the law, but it may not always be able to provide a meaningful remedy to the party found to be right").

[8] See E. Keith Stott. Jr., and Richard N. Ross, infra note 11, noting (P. 39) that "… filing fees are necessary to deter frivolous litigation or to channel different types of cases to appropriate courts or other nonjudicial dispute resolution forms, such as counseling, mediation, or arbitration."

ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛል የሚል ጽኑ እምነት አለ፡፡ የዳኝነት አገልግሎት የሚያገኙ ተከራካሪ ወገኖች ቀደም ሲል ሲሠራበት እንደቆየው ሁሉ (አሁን ያለውን የብር የመግዛት አቅም ባገናዘበ ሁኔታ) የመንግሥትን ጫና ማገዝ አለባቸው የሚለው ምክንያት የቆየውን ሕግ ለመለወጥ እንደ አንድ ሌላ አሳማኝ ምክንያት የተወሰደ መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በላይ በተገለጹት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሳ ቀደም ሲል የነበረውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሕግ ለመቀየር ሲታሰብ ሌላው ከግምት ውስጥ የገባው ፍሬ ነገር የክልሉ ኅብረተሰብ አጠቃላይ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ነው፡፡ በደንቡ መግቢያ ላይ እና በዝርዝር ድንጋጌዎቹ ላይ በግልጽ ተመልክቶ እንደምናገኘው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በምንም ምክንያት ይሁን የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት (Right of every individual to Access to Justice) የሚገድብ እንዳይሆን የክልሉ ኅብረተሰብ አጠቃላይ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በሚገባ ተመዝኗል፡፡ በኢኮኖሚ ዝቅተኛ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል፣ በማኅበራዊ ኑሮም ለልዩ ልዩ ጥቃቶች ወይም መድሎዎች ተጋላጭ የሆኑ፣ በዕድሜ፣በጾታ፣ በአካላዊ ሁኔታ፣ በጤና፣ ...ወዘተ በመሳሰሉት ምክንያት ልዩ ድጋፍና ማበረታቻን የሚጠይቁ የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ፍርድ ቤት የሚያስመጣ የክስ ምክንያት ቢኖራቸው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያው መሰናከል ወይም እንቅፋት እንዳይሆናቸው ጥንቃቄ ተደርጎ በአንጻሩ ለዳኝነት አገልግሎት መክፈል የሚችሉት ግን የመንግሥትን ጫና እንዲጋሩ በግልጽ ተመላክቷል፡፡ በቆየውና አሁን ድረስ በሚሠራበት የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ (በክልሉ ተቀባይነትን አግኝቶ እየተሠራበት ያለ) በግልጽ እንደተመለከተው የዳኝነት አገልግሎት ለመክፈል የሚያስችል ገንዘብ የሌላቸው ሰዎች በደሃ ደንብ መሠረት ያለክፍያ እንዲከራከሩ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም ባሻገር የክልሉን ኅብረተሰብ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አኗኗር እንዲሁም ሌሎች ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ ከዚህ በፊት በነበረው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሕግ ላይ ያልተካተቱ አዳዲስ ነገሮች በደንቡ አንቀጽ 7 ሥር "የዳኝነት ክፍያ ስለማይከፈልባቸው ክሶች" በሚል በርከት ያሉ የክስ ምክንያቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

አንዳንድ ሰዎች በደንቡ ውስጥ የሰፈሩ እንዲህ ዓይነት የፍትሕ ተደራሽነትን የሚያሰፉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን በሚገባ ሳይመለከቱ እንዲሁ በጥቅል አነጋገር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠኑ መጨመሩ የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚገድብ ነው የሚሉት መሠረተ-ቢስ ነው፡፡ ደሃ ለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ አስቀድመህ ካልከፈልክ ተብሎ የማይከለከል ከመሆኑም በላይ ከዚህ በፊት ተደርጎ በማያውቅ ሁኔታ ደሃ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ያለምንም የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ክስ ማቅረብ የሚቻልባቸው በርከት ያሉ ጉዳዮች መካተታቸው ሊታወቅ ይገባል፡፡ የዚህ አዲስ ደንብ መውጣት ከዚህ ቀደም በነበረው ሕግ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችሉ የነበሩትን በርካታ አቤቱታ አቅራቢዎች በነጻ ማቅረብ እንዲችሉ በር የሚከፍት እንደሆነ የደንቡን አንቀጽ 6 እና 7 በማንበብ መረዳት ይቻላል፡፡ ዝርዝሩ ከዚህ በታች የሚቀርብ ቢሆንም ለማሳያ ያህል፡-

- በሕፃን ሞግዚት የሚቀርብ የወላጅነት ይታወቅልኝ ወይም የልጅ አስተዳደግን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ፤
- በቤተሰብ ሕግ መሠረት በማንኛውም ሰው የሚቀርብ የቀለብ ይወሰንልኝ አቤቱታ፤
- ከውል ውጭ በሚደርስ የሞት ወይም የአካል ጉዳት ጋር በተያያዘ በተጎጅ ወይም በተጎጅ ጥገኞች የሚቀርብ በቀለብ መልክ የሚከፈል ካሣ አቤቱታ፤
- በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋዊያን እና ሌሎች ልዩ ድጋፍን በሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ ላይ የሚቀርብ የወል የሰብአዊ መብቶች የማስከበር አቤቱታ፤ ... ወዘተ

የመሳሰሉት አቤቱታ አቅራቢዎች በነጻ ማቅረብ እንዲችሉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህ እንግዲህ በፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕጉ በተመለከተው አግባብ ደሃ ለመሆኑ ማስረጃ በማቅረብ በትክክልም ደሃ ስለመሆኑ በማስረጃ ያረጋገጠ ወገን በነጻ

እንዲከራከር በደንቡ አንቀጽ 6 (1) (ሀ) ከተፈቀደው በተጨማሪ የደሃነት ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልግ ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ሆኖ አቤቱታ ማቅረብ የተፈቀደ መሆኑን የሚያሳይ አዲስ ድንጋጌ ነው፡፡

### 2.1. ደንቡ እንዴት ተዘጋጀ?

ይህ አዲስ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ የተዘጋጀው ከዚህ በፊት የነበረውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ሕግ፣ ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ትርጓሜ የሰጠበትን፣[9] በክልሉ ውስጥ ያሉ ፍርድ ቤቶችን ተግባራዊ ተሞክሮ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ ረቂቅን፣ የኦሮሚያ እና የሐረሪ ክልላዊ መንግሥታት ዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንቦችን እንዲሁም የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በማገናዘብ ጭምር ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ የተደረጉ ውስን የሀገር ውስጥ[10] እና የውጭ ሀገራት[11] የጥናትና ምርምር ሥራዎችም በማገናዘቢያነት ውለዋል፡፡ በተለይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአቶ ገብሩ ኮሬ እና አቶ አመዲዮ ፋዴሬቼ፣ የሰ/መ/ቁ የሰ/መ/ቁ. 52942 ጥቅምት 18 ቀን 2003 የሰጠው ፍርድ ላይ ያካተተው ሀሳብ መሠረታዊ በመሆኑ ደንቡ በሚረቀቅበት ወቅት ከፍተኛ ትኩረትን የሳበ ነበር፡፡ በዚህ ፍርድ ላይ የተካተተው ሀሳብ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> አንድ ሰው በፍርድ ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይን ፍርድ ቤት ይዞ ሲቀርብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል ያለበት መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 215፣ ከ467 እስከ 479 ድረስ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡ የዳኝነት አገልግሎት መክፈል የማይችል ሰው ክስ ለማቅረብ የሚችልበት አግባብ ስለመኖሩም ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ አንድ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመክፈል የማይችል ሰው በደሃ ደንብ ክስ ለማቅረብ የሚችል ሲሆን ለመክፈል አቅም ያለው ክስ ያቀረበ መሆኑ ከተረጋገጠ ግን መዝገቡ እንደሚዘጋ፣ የተዘጋ መዝገብ ደግሞ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ/ገንዘቡን/ ለመክፈል ዝግጁ እስከሆነ ድረስ የሚንቀሳቀስለት መሆኑን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መንፈስና ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡[12]

---

[9] ለምሳሌ *ዋዜማ የልብስና ሸራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት*፣ የሰ/መ/ቁ 17352፣ ሐምሌ 28 ቀን 1997 የተሰጠ ፍርድ (ሰበር ውሳኔዎች ቅጽ 1)፣ ገጽ 18-23፣ አቶ ገብሩ ኮሬ እና አቶ አመዲዮ ፋዴሬቼ፣ የሰ/መ/ቁ የሰ/መ/ቁ. 52942 ጥቅምት 18 ቀን 2003 የተሰጠ ፍርድ (የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ውሳኔዎች፣ ቅጽ 12)፣ ገጽ 305፣ *አበባዬ አቢ ደራወርቅ እና ይገረም ፈዩ*፣ የሰ/መ/ቁ 46281፣ ታህሳስ 28/2003 የተሰጠ ፍርድ (ሰበር ውሳኔዎች ቅጽ 12) ፣ገጽ 320-321፣ *ቤተልሄም ፋርማሲቲዩካል ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ*፣ የሰ/መ/ቁ. 79555 ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠ ፍርድ (የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ውሳኔዎች፣ ቅጽ 14)፣ ገጽ 133-134፣ *ወ/ት ፍሬወይኒ አለም (ሶስት ሰዎች) እና አቶ አለም መሐሪ*፣ የሰ/መ/ቁ 86454፣ግንቦት 23/2005 የተሰጠ ፍርድ (ሰበር ውሳኔዎች ቅጽ 15)፣ ገጽ 156- …፣ ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኅበር፣ የሰ/መ/ቁ 27574፣ ጥቅምት 26/2000 የተሰጠ ፍርድ (ሰበር ውሳኔዎች ቅጽ 7)፣ ገጽ…፣ *ወ/ሮ ሰሚራ ጀማል እና አቶ ናስር ሐጎስ*፣ የሰ/መ/ቁ 188406 መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ/ም የተሰጠ ፍርድ (ገና ያልታተመ)፣ … ወዘተ፡፡

[10] Belay Tizazu Mengistie," Socioeconomic and legal analysis of court fees structure and payment system in Ethiopia: Towards a policy-oriented approach", 5*(2) Journal of Socioeconomics and Development (2022)*, PP. 175-187; Kahsay Giday, "Allocation of Costs and Fees of Civil Litigation in Federal Supreme Court Cassation Division: Does One Approach Really Fit All'?", *7 (1) Oromia Law Journal (2018),* PP.24-40; Tajebe Getaneh, "Introducing Third-Party Litigation Funding in Ethiopia: Implications for Enhancing Access to Justice", 11 (2) Bahir Dar University J. L. (June 2021),PP. 141-168;

[11] E. Keith Stott. Jr., and Richard N. Ross, "Survey and Analysis of Court Filing Fees", 2 (2) *State Court Journal (Spring 1978)*, PP. 8-43, available at: https://www.ojp.gov/pdffiles1/Digitization/47398NCJRS.pdf.; Hugh D. Spitzer, "Taxes vs. Fees: A Curious Confusion", 38 Gonz. L. Rev. (2002), PP. 335-365 (to note the distinction between taxes and fees); William Severson, "Tax or Fee? A Proposed Framework For Deciding When State Constitutional Tax Limitations Apply", 41 Gonz L. Rev. (2021/22), PP. 43-100 (distinction between taxes and fees); Radyshevska Olesya R., "Court fee system in Ukraine and in selected Member State of the EU- General Comparative Analyses," Administrative Law and Process, 3(Ювілейний) (2019) 198-207 (For the experience of Ukraine and a number of other countries) available at: https://applaw.net/index.php/journal/article/view/403.; Rafael Mery Nieto, "Court Fees: Charging the User as a Way to Mitigate Judicial Congestion", *1 (1) The Latin American and Iberian Journal of Law and Economics, Article 7 (2015)*, PP 109-119, Available at: http://laijle.alacde.org/journal/vol1/iss1/7.

[12] አቶ ገብሩ ኮሬ እና አቶ አመዲዮ ፋዴሬቼ፣ የሰ/መ/ቁ የሰ/መ/ቁ. 52942 ጥቅምት 18 ቀን 2003 የተሰጠ ፍርድ (የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ውሳኔዎች፣ ቅጽ 12)፣ ገጽ 305፡፡

ይህ መሠረታዊ ሀሳብ በደንቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶታል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ለሚያገኙት የዳኝነት አገልግሎት ተገቢውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል አለባቸው የሚለው በሁሉም ሀገር ባይባል እንኳ (ከሉግዘንበርግ በስተቀር[13] እና ስፔንና ፈረንሳይ ካላቸው ልል አቋም/ዝቅተኛ ክፍያ ሥርዓት በስተቀር) በአብዛኛዎቹ የዓለም ሀገራት ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ነው፡፡ በኢትዮጵያም የቆየው ሕግና አሠራር ሆነ አሁን በአዲሱ ደንብ የተካተተው እንደዚሁ ተመሳሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍርድ ቤት በሌላ መንገድ እንዲወስን የሚያደርግ አሳማኝ ምክንያት እስካልቀረበ ድረስ ይህን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል ያለበት ከሳሹ ወገን እንደሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአበባዬ አቢ ደራወርቅ እና ይገረም ፈዬ[14] የሰጠው አስገዳጅ ትርጓሜ ማለትም "የዳኝነት ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የከሣሹ ወገን እንደሆነ" የገለጸው በደንቡ አንቀጽ 6 (1) ውስጥ በግልጽ ተካትቷል፡፡ ከከሳሽ ውጭ የሆነና ፍርድ ቤት ዳኝነት እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሌላ የክርክር ተካፋይ ለምሣሌ የተሰጠ ፍርድ ጥቅሜን ወይም መብቴን ነክቷል ሲል ፍርድ እንዲነሳለት የሚጠይቅ ሰው እንዲሁም የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የሚያቀርብ ወገን የዳኝነት አገልግሎት የመክፈል ግዴታ አለበት የሚለው ሁሉ በግልጽ ተካትቷል፡፡

**2.2. በደንቡ ላይ ውይይት ስለመደረጉና ግብዓቶች የተሰበሰቡበት ስለመሆኑ**

የክልሉ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ ከመጽደቁ በፊት በረቂቁ ላይ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተለያዩ መድረኮች ውይይት የተደረገበትና አስተያየት የተሰጠበት፣ ልዩ ልዩ ግብአቶች ሁሉ የቀረቡበት ነበር፡፡ በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ መድረክ ከተሳተፉትና ግብአት ከሰጡት መካከልም፡-

- የሚመለከታቸው የዳኝነት እና ሌሎች የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች፣
- የሕግ ባለሙያዎች ማሠልጠኛ እና ምርምር ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች፣አሰልጣኞችና ተመራማሪዎች፣
- የጠበቆች ተወካዮች፣
- የክልሉ ምክር ቤት የሕግ፣ፍትሕ እና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ፣
- የክልሉ ምክር ቤት እና የመስተዳድሩ የሕግ አማካሪዎች፣ ይገኙበታል፡፡

የተሳታፊዎች ስብጥር ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሀሳብ ለማሰባሰብ ያስቻለ ሲሆን በተለይ ደግሞ ጉዳዩ ላይ የቀረበ ተጨባጭ ተሞክሮውና ዕውቀቱ ያላቸው የዳኝነት እና ሌሎች የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች፣ የሕግ ባለሙያዎች ማሠልጠኛ እና ምርምር ኢንስቲትዩት የሥራ ኃላፊዎች፣አሰልጣኞችና ተመራማሪዎች እንዲሁም የጠበቆች ተወካዮች የሰጡት ግብዓት የደንቡን ይዘት ለማዳበር ያስቻለ ነበር፡፡ በሌላ ወገንም የሕዝብ ወኪል የሆኑ የክልሉ ምክር ቤት የሕግ፣ፍትሕ እና አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም የክልሉ ምክር ቤት እና የመስተዳድሩ የሕግ አማካሪዎች ተገኝተው አስተያዬትና ግብአት የሰጡበት ይዘቱን የበለጠ ለማዳበርና የሁሉንም ወገን እይታና ድጋፍ ለማካተት ይደረግ የነበረውን ጥረት ያሳካ ትልቅ ትርጉም የነበረው ነው፡፡

**3. የደንቡ ዓላማዎች**

ደንብ ቁ 17/2017 እንዲወጣ የተደረገበት ዓላማ በራሱ በደንቡ ላይ በግልጽ የተመለከተና ማብራሪያ የማይጠይቅ ነው፡፡ አንቀጽ 4 እንደሚደነግገው የደንቡ ዋና ዋና ዓላማዎች፡-

---

[13] See Mario Di Stefano, "Study on the Transparency of Costs of Civil Judicial Proceedings in the European Union", Luxemberg, Country Report (December 30, 2007), P.9; available at: https://e-justice.europa.eu/sites/default/files/2012-12/cost_study_luxembourg_LU_en.pdf.

[14] አበባዬ አቢ ደራወርቅ እና ይገረም ፈዬ፣ የሰ/መ/ቁ 46281፣ ታህሳስ 28/2003 የተሰጠ ፍርድ (ሰበር ውሳኔዎች ቅጽ 12) ፣ገጽ 320-321፡፡

- ፍርድ ቤቶች ለሚሰጡት አገልግሎት የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት በማይጋፋ መልኩ ተመጣጣኝ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዲያስከፍሉ ማስቻል፤
- አጠቃላይ የዳኝነት አገልግሎቱን ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ፣ ጥራት ያለው እና ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል፤
- የክስ ምክንያት የሌላቸው፣ከፍርድ ቤት ውጭ ማለቅ የሚችሉ እንዲሁም ከቅን ልቦና ውጭ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በመቆጣጠር ለዳኝነት ሥራ አካሄድ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻል፤

ናቸው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ከፍ ሲል ደንቡን ለምን ማውጣት እንዳስፈለገ ስንገልጽ ከነበረው ጋር አገናዝቦ ማዬት ይገባል፡፡

አንዳንድ ሰዎች አዲሱን ደንብ ለምን ማውጣት እንዳስፈለገ እና በአዲሱ ደንብ ለማሳካት የተፈለገው ምን እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው በአንድ በኩል የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጨመሩን ቁጥሩን ማለትም የገንዘብ መጠኑን ብቻ በማዬት በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ነዋሪ ኅብረተሰብ ባለፉት ተከታታይ አመታት ሆነ አሁን ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ (ጦርነት፣ ግጭትና መፈናቀል፣በአጠቃላይም የሠላም እጦትና የደኅንነት ሥጋት) እንዲሁም የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ወይም ድቀት በማዬት አሉታዊ ትችት ሲያቀርቡ ይሰማሉ፡፡ ይህ ግን በሌላ ገጽታውም መታዬት ያለበት ነው፡፡ በእንዲህ ዓይነት ችግር ውስጥ በሚገኝ ኅብረተሰብ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው በተቻለ መጠን ያሉትን አለመግባባቶች በራሱና በአቅራቢያ በሚያገኛቸው ሠላማዊና ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ፣ ኃይማኖታዊ እና ሌሎች አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች ለመፍታት መጣርና ጊዜውን፣ጉልበቱንና ያለ አንጡራ ሀብቱን ለምርት ሥራ (ግብርና፣ንግድ እና ሌሎች የኢኮኖሚ እድገትን የሚያመጡ መስኮች) ላይ ማዋል ይገባዋል፡፡ ትንሹንም ትልቁንም ጉዳይ፣ የማያዋጣውንና የሚያዋጣውን ጉዳይ፣ በሌሎች አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች ሊፈቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ሁሉ በፍርድ ቤት ፊት በማቅረብ በክርክር ሂደት ጊዜን፣ጉልበትን እና አንጡራ ሀብትን ማባከን እንዳይኖር በማስተዋልና አርቆ በማሰብ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በተለይም በእልህ፣በአልሸነፍ ባይነት እስከመጨረሻ ፍርድ ሰጭ አካላት የሚደረግ ክርክር ለበለጠ ወጭና ለማኅበራዊ መስተጋብር መበላሸት የሚዳርግ ስለሆነ ቆም ብሎ ራስን መፈተሽ የሚጠይቅ ነው፡፡ በአንዳንድ ክርክሮች ላይ በመጨረሻ ረች ተብሎ የሚያጠናቅቀው ተከራካሪ ወገን ምናልባት ድምር ውጤቱ ቢመዘን በገንዘብ ሲሰላ ወጭ የሚያመዝንበት፣ ከመደበኛ ሥራ ርቆ በፍርድ ቤት ፊት ለክርክር ያባከነው ጊዜና ጉልበት የበለጠ የኢኮኖሚ ዕድገትን ሊያመጣ የሚችልበትን ያስቀረ ወይም የቀነሰ፣ ከቤተሰብ፣ጎረቤት ወይም ማኅበረሰብ ጋር የነበረውን መልካም ትስስርና መረዳዳት ያሻከረበት ወይም ጠላት ያፈራበት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሲባል ግን የግድ መከበርና መጠበቅ ያለበትን ጥቅም ወይም መብት ለማረጋገጥና ተፈጻሚ ለማድረግ ተወደደም ተጠላ ወደ ፍርድ ቤት መሄድን የሚጠይቁ እንዳሉ ሳንዘነጋ ነው፡፡

በአዲሱ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ እነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ከግምት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ምንም እንኳ ተከራካሪ ወገኖች ከሌላው ሰው በተለዬ በፍርድ ቤቶች ፊት ቀርበው ለሚያገኙት የዳኝነት አገልግሎት መጠነኛ ገንዘብ በመክፈል የመንግሥትን ወጭ እንዲጋሩ ቢደረግም ይህ ክፍያ ግን ከአገልግሎት ክፍያ (court fee) ያለፈ እንዳልሆነ በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የአገልግሎት ክፍያ ልክ እንደ ግብር ወይም ታክስ ወይም ደግሞ እንደ የጉዳት ካሣ መተኪያ ወይም ደግሞ ሌላ የገቢ መሰብሰቢያ ስልት የሚወሰድ አለመሆኑ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ይህ ደንብ የመንግሥትን የገቢ አቅም ለመጨመር ተብሎ የወጣ አይደለም፡፡ የዳኝነት አገልግሎት መንግሥት በመንግሥትነቱ ለኅብረተሰቡ የሚሰጠው ሕዝባዊ አገልግሎት ስለመሆኑ ግልጽ ግንዛቤ ተይዞ የወጣ ሕግ ነው፡፡ ረቂቁ በሚዘጋጅበት ወቅት ሆነ በሚጸድቅበት ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የመንግሥትን ወጭ በመጠኑ ከመጋራት ያለፈ አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ፍላጎት ያሳየ ቀርቶ አስተያየት እንኳ ያቀረበ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳይገድብ ከፍ ያለ ጥንቃቄ እንዲደረግ ነው ግብአቶችና አስተያዬቶች ሲሰነዘሩ የነበረው፡፡ በመሆኑም ደንቡ የተዘጋጀው የክልሉን ኅብረተሰብ

ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በሚገባ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም አንቀጽ 6 እና 7 የሚደነግጉትን በማዬት መረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ሰው ደሃ በመሆኑ ምክንያት ፍትሕ የማግኘት መብቱ እንዳይገደብ ግልጽ ድንጋጌ ከማካተት ባሻገር ደሃ መሆንን ማረጋገጥ ሳያስፈልግ በነጻ መከራከር እንዲችሉ የተፈቀደላቸው ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከሚፈጸመው በደል ወይም የመብት ጥሰት በመነሳት ብቻ በርካታ የክስ ዓይነቶች በነጻ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥባቸው እንዲሆኑ  በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት በገጠር የሚኖረው የክልሉ ኅብረተሰብ ወደ 87% የሚጠጋ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡ በፍርድ ቤቶች ፊት የሚቀርበው የፍትሐ ብሔር እና የወንጀል ጉዳይም በአመዛኙ የገጠር ሰው ተከራካሪ የሆነበት ነው፡፡ በተለይ የሚበዛው ጉዳይ ደግሞ የመሬት ይዞታንና ከመሬት የመጠቀም መብት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በደንቡ አንቀጽ 11 ላይ እንደሚታየው በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶችን (ለምሳሌ እንደ ሁከት ይወገድልኝ እና የመሳሰሉት ከመሬት ይዞታና በመሬት የመጠቀም መብት ጋር የተያያዙ) በተመለከተ የተደነገገው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ቀደም ሲል ከነበረው የብር የመግዛት አቅም ጋር ተመዛዝኖ ሲታይ እንዲሁም በክርክሩ ውስጥ ካለው ጥቅም ወይም መብት አንጻር ሲመዘን በጣም ዝቅተኛ የሚባል ካልሆነ በስተቀር የተጋነነ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ባለፉት 40፣50፣60 እና 70 አመታት በነበረው ዳኝነት አገልግሎት መወሰኛ ሕግ መሠረት ብር 25 ይከፈልበት የነበረው አሁን በአዲሱ ደንብ በወረዳ ፍርድ ቤት ፊት ሲቀርብ ብር 1,000 (አንድ ሽህ ብር) እንዲከፍልበት መደንገጉን ማዬት ይቻላል፡፡ የዛሬ ሃያ ወይም ሠላሣ አመት በፊት 25 ብር ምን ሊገዛ እንደሚችልና በአሁኑ ወቅት 1,000 ብር ምን ሊገዛ እንደሚችል ለሚያመዛዝን ሰው የተደረገው ጭማሪ ከዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ ሊረዳ ይችላል፡፡ የፌዴራሉ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ ከገጠር መሬት ይዞታና ከመሬት አጠቃቀም ጋር የሚነሱ ጉዳዮች እምብዛም ስለማይመለከቱት - ከግዛት (territorial area) አንጻር በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች የተወሰነ ስለሆነ- ከእነዚህ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚመለከት ድንጋጌ አልያዘም፡፡ በአንጻሩ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ ቁ 8/2016 ግን እነዚህንና ሌሎች ከመሬት ይዞታ፣ የመሬት አጠቃቀም፣.. ወዘተ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አስመልክቶ የዳኝነት አገልግሎት እንደሚከፈልና የክፍያ መጠኑ እንዴት እንደሚሰላ በአንቀጽ 12 (1) (ሐ)፣ 12 (2)፣12 (3) (ሀ)እና (ለ) በዝርዝር ደንግጓል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ የመሬት ባለይዞታነት ክስ ዳኝነት ከተጠየቀበት ጥቅም አንጻር ተሰልቶ የዳኝነት አገልግሎት እንዲከፈልበት የተወሰነ ሲሆን ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ ይህ ጥቅም የሚሰላው ክሱ ከቀረበበት አንድ አመት አስቀድሞ መሬቱ ያስገኘው ገቢ ላይ በመመርኮዝ፣መሬቱ ክስ ከቀረበበት አንድ አመት አስቀድሞ ምርት ያልሰጠ እንደሆነ የመሬቱ አዋሳኝ የሆነ ሌላ ክሱ እንደቀረበበት ያለ ተመጣጣኝ መሬት ክሱ ከቀረበበት አንድ አመት አስቀድሞ ያስገኘው ገቢ ላይ በመመርኮዝ መከፈል ያለበት የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ስሌት መከፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የአማራ ክልል ደንብ ቁ 17/2017 ግን በአንቀጽ 12 (2) ሥር የመሬት ይዞታን፣ የመሬት አጠቃቀምን፣ የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ መሬት ላይ በአላባ ወይም በሌላ ሕጋዊ መንገድ መጠቀምን፣ በሌላ ሰው የይዞታ መሬት ላይ የሚጠየቅ እንደመተላለፍ መብት እና እይታን ያለመከልከል መብትን፣... የመሳሰሉ ከ(ሀ)-(ሸ) የተጠቀሱ ጉዳዮች የዳኝነት ክፍያ መጠንና ስሌት አስመልክቶ ወደፊት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥናትን መሠረት አድርጎ በሚያወጣው መመሪያ እንደሚመለስ ደንግጎ እስከዚያው ድረስ ግን በገንዘብ ሊገመቱ በማይችሉ ክሶች እንደሚቀርብበት የፍርድ ቤት እርከን ተለያይቶ እንዲከፈል በሚል በቁርጥ የገንዘቡ መጠን በወረዳ ፍርድ  ቤት ሲሆን ብር 1,000፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ብር 1,500 እና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን ደግሞ ብር 2,000 ተብሎ ተደንግጓል፡፡

ከላይ የተጠቀሱ ምሳሌዎችና ኦሮሚያ ክልል ተሞክሮ የቀረበው በአማራ ክልል የተደረገው ጭማሪ አንዳንዶች እንደሚሉት የተጋነነ አለመሆኑን ለማሳዬት ያህል እንጅ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠንን ለመወሰን ከግምት ውስጥ የሚገቡት በርካታ

ፍሬ ነገሮች እንዳሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡[15] በክርክሩ ውስጥ ያለው ጥቅም/ሙብት ስፋት፣ በገንዘብ የሚተመን ከሆነም የያዘው የገንዘብ መጠን፣ የክርክሩ ውስብስብነት ወይም ቀላልነት፣ ክርክሩን ለመቋጨት የሚወስደው ጊዜ፣ጉልበትና ወጭ፣ ... የመሳሰሉት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ናቸው፡፡ ከዚህ ሌላም የሚጠየቀው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ሰዎች በቀላሉ ጉዳይ ሁሉ ወደ ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ የሚገፋፋ በርን የመክፈት ዕድሉ ወይም ደግሞ በተቃራኒው ፍትሕ የማግኘት ሙብትን የሚከለክል ወይም የሚገድብ የመሆን ዕድሉ ሁሉ ታሳቢ ይደረጋል፡፡ የኅብረተሰቡ የተከራካሪነት ባህልም አንዱ ታሳቢ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ሌላውና በዋነኛነት በብዙ ሀገሮች ከግምት ውስጥ እንዲገባ የሚደረገው የሚጠየቀው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን በፍርድ ቤቶች የፍርድ መዛግብት ክምችት እና በፍርድ ቤቶች የሥራ ጫና ላይ ያለው አንድምታ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ከግምት ውስጥ ገብተውና በሚዛን ታይተው የሚወሰን እንጅ እንዲሁ ዝምብሎ በዘፈቀደ ከሆነ የገንዘብ መጠን ላይ ጀምሮ ከፍ ያለ ወይም ያነሰ የክፍያ መጠን የመወሰን ጉዳይ አይደለም፡፡ በአማራ ክልል የወጣው አዲስ ደንብ ይዞት የወጣው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን የተጋነነ ነው ለማለት የትኛው መመዘኛ ፍሬ ነገር ተወስዶ እንዲህ ዓይነት መደምደሚያ ላይ እንደተደረሰ ባልተገለጸበት ሁኔታ የሚሰጥ አስተያዬት ውሃ የሚቋጥር ሆኖ አይታይም፡፡ ይልቁንም ከፍ ሲል የተጠቋቆሙ መመዘኛዎችን እና ደንቡ ሊያሳካ የፈለጋቸውን ዓላማዎች በአግባቡ ለሚመዝን ሰው ይህ ደንብ ሊያሠራ የሚችል የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ይዞ እንደመጣ ሊገነዘብ ይችላል፡፡

## 4. በደንቡ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች

የክልሉ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ በርካታ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ

- የደንቡ የተፈጻሚነት ወሰን፣
- የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የመክፈል መርሕ፣
- ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ስለሆኑ ሰዎችና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይከፈልባቸው ክሶች፣
- በደሃ ደንብ መሠረት በነጻ ስለሚደረግ ክርክር እና በክርክር መጨረሻ ስለሚኖር የክፍያ ሁኔታ፣
- የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ስለሚከፈልበት ጊዜ እና የአከፋፈል ሥርዓት፣
- በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች እና በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠንና የሥሌት ዘዴ፣
- ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈል ክፍያና መጠን፣
- ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት እና
- የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ናቸው፡፡

እነዚህን ከዚህ በታች አንድ በአንድ በአጭሩ እንዳስሳለን፡፡ ትርጓሜ ከሚሰጠው ድንጋጌ ጀምሮ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች በእነዚሁ ዋና ዋና ጉዳዮች አንጻር ወይም ከእነዚህ በአንዱ ወይም በሌላው ስር የሚጠቀሱ ይሆናል፡፡

### 4.1. የደንቡ የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዲስ የዳኝነት አገልግሎት ሕግ ተፈጻሚነት ወሰን በደንቡ ውስጥ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ካላቸው የታወቀ/ተፈጥሯዊ ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣን (inherent regional judicial power) ባሻገር ከፌዴራሉ ሕገ-መንግስት የመነጨ የፌዴራል ጉዳዮችን በውክልና የማየት ሥልጣን (constitutionally delegated federal judicial power) ያላቸው በመሆኑ በዚህ ረገድ ሊፈጠሩ የሚችሉ መደናገሮችን ሁሉ ሊቀርፍ በሚችል መልኩ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት

[15] ከላይ በግርጌ ማስታዎሻ ቁጥር 11 ስር የተመለከቱ የጥናት ውጤቶችን ይመለከቷል፡፡

አንቀጽ 3(1) ሥር የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጥበት ለክልሉ ፍርድ ቤቶች በሚቀርብ ማንኛውም ክስ ላይ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በንዑስ አንቀጽ (2) ሥር ደግሞ የንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚመለከቷቸውን የፌዴራል ጉዳዮች በሚመለከት የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተደንግጎ እናገኛለን፡፡ በመሆኑም አንድ ለፍርድ ቤት በቀረበ ጉዳይ ላይ የሚከፈለውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ለመለዬት እንዲሁም ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ ለሚነሳ ማናቸውም ዓይነት ጥያቄ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕግ የክልሉ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ደንብ ወይም ደግሞ የፌዴራሉ የዳኝነት ክፍያ ደንብ ስለመሆኑ ለመወሰን በቅድሚያ የቀረበው ጉዳይ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የታወቀ/ተፈጥሯዊ ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወይም በውክልና ሥልጣን የሚስተናገድ የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ መለየት ይኖርበታል፡፡ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የታወቀ/ተፈጥሯዊ ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ጉዳይ ከሆነ ተፈጻሚነት የሚኖረው የክልሉ ደንብ ቁጥር 17/2017 ነው፡፡ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በውክልና ሥልጣን የሚታይ ጉዳይ ከሆነ ግን አንደዚሁ በቅርብ ጊዜ በፌዴራሉ ሕግ አውጭ ማለትም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክፍያን ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 1/2017 ዓ.ም[16] ነው፡፡ ይህን ልዩነት በመገንዘብ እንደየአግባብነቱ የክልሉ ደንብ እና የፌዴራሉ ደንብ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይገባል፡፡

ከተፈጻሚነት ወሰን ጋር በተያያዘ ሌላው ልብ ሊባል የሚገባ ጉዳይ ደንብ ቁ 17/2017 አንቀጽ 3 (3) ሥር የተደነገገው ነው፡፡ ይኸውም ደንቡ "ለፍርድ ቤት በሚቀርብ የአስተዳደራዊ ጉዳይ አቤቱታ ላይ ተፈጻሚነት የለውም" በሚል የተደነገገው ነው፡፡ በፍርድ ቤት ክርክር ያላቸው ሰዎች ሆኑ ሌሎች ክርክር የሌላቸው ሰዎች በተለያዩ ምክንያት ከዳኝነት ሥራ/አገልግሎት ውጭ የሆኑ ጥያቄዎችን ለፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ሥራ መሪዎች ያቀርባሉ፡፡ በተከፈተ የፍርድ ቤት መዝገብ ላይ ዳኝነት የሚሰጥበት ሳይሆን በአመራር ኃላፊነት ላይ በሚገኙ ሰዎች አስተዳደራዊ በሆነ መንገድ የገጠማቸው ችግር እንዲፈታ በጽሑፍ (በሰነድ) የተዘጋጀ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ የወረዳ ፍርድ ቤት/የከፍተኛ ፍርድ ቤት/የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት/የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ችሎት፣ የኮንስትራክሽን ችሎት፣ የወረዳ/የከፍተኛ/የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር፣መዝገብ ቤት ሠራተኛ፣ ችሎት ጸሐፊ፣... ወዘተ እንዲህ ያለ በደል ስለፈጸመብኝ፣ በአግባቡ ሊያስተናግደኝ ስላልቻለ፣...ወዘተ በበላይ አመራሩ ርምጃ ይወሰድልኝ የሚል አስተዳደራዊ አቤቱታ ሲቀርብ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ አይጠየቅበትም፡፡

እንዲሁም የፍርድ ቤት ሠራተኞች ሆኑ ዳኞች ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ወይም ለሌላ ኃላፊ በጽሑፍ የዝውውር፣የቤት አበል፣የሕክምና፣ የዕረፍት፣.... ወዘተ ጥያቄ ቢያቀርቡ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ክፈሉ ሊባሉ አይችሉም፡፡ ከአስተዳደር ኃላፊዎች የሚሰጥ ደብዳቤ ቢኖርም ለደብዳቤው የአገልግሎት ክፍያ ፈጽሙ ሊባሉ አይችሉም፡፡ በአጭሩ የደንቡ ተፈጻሚነት ለሚጠዬቅ የዳኝነት ሥራ (judicial functions) ወይም የዳኝነት አገልግሎት (judicial services) እንጅ ለማንኛውም አስተዳደራዊ ሥራና አስተዳደራዊ ውሳኔ አይደለም፡፡ ይህ ጉዳይ ከሌላ አስተዳደራዊ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነገር ግን በፍርድ ቤት ፊት የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር መምታታት የለበትም፡፡

በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔውን በሙሉ ወይም በከፊል በመቃወም ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ይከለስልኝ ወይም በይግባኝ ይታረምልኝ ሲል ከሚያቀርበውና የዳኝነት ሥራን/የዳኝነት አገልግሎትን ከሚጠይቅና በመዝገብ

[16] የዚህ ደንብ አጭር ርዕስ ወይም ስያሜ በደንቡ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተው "የዳኝነት ክፍያ ደንብ ቁጥር 1/2017" የሚል ነው፡፡ ደንቡ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ 31ኛ ዓመት፣ቁጥር 41 ሆኖ ሚያዝያ 29 ቀን 2017 ዓ/ም ታትሞ የወጣና ከዚሁ ቀን ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለ ነው፡፡ የተሰጠው አጭር ስያሜ (ርዕስ) በአማራ ክልል ሆነ በሌሎች ክልሎች (ለምሣሌ በኦሮሚያ እና በሐረሪ ክልላዊ መንግሥታት) ከወጡት ጋር እንዳያምታታ በዚህ ጽሑፍ "የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ" በሚል ይጠቀሳል፡፡ በሌላ በኩል በእንግሊዝኛው ቅጅ (English Version) የደንቡ ቁጥር "1/2024" የተባለው ተራ ግድፈት/ስህተት በመሆኑ Federal Courts Court Fee Regulation No 1/2025 በሚል መወሰድ ያለበት ነው፡፡

ላይ ከሚሠራ ጋር ማምታታት አይገባም፡፡ የአስተዳደራዊ ውሳኔን በይግባኝ ለማሳረም (Appeal) ወይም በክለሳ ለማስተካከል/ለማሻር (Review) የሚቀርብ አቤቱታ የዳኝነት ሥራ/አገልግሎት አካል በመሆኑ ከአስተዳደራዊ ጉዳይ አቤቱታ ይለያል፡፡ በዚህ ረገድ መደናገር እንዳይኖር የደንቡ አንቀጽ 2 (6) “የአስተዳደራዊ ጉዳይ አቤቱታ” ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ሰጥቷል፡፡ ይኸውም “አስተዳደራዊ መፍትሔ እንዲሰጥ፣እርምት እንዲደረግ ወይም አስተዳደራዊ መመሪያ እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት በቃል፣ በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን መገናኛ ዘዴ የሚቀርብ ማመልከቻ ነው” ሲል ይተረጉመዋል፡፡

### 4.2. የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መክፈል መርሕ

በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ተሞክሮ በተግባር ከፍተኛ ብልሽትና የአሠራር መደበላለቅ ከሚታይባቸው ጉዳዮች አንዱ የነበረው ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ አፈጻጸም ጋር የሚታየው ነበር፡፡ በርካታ ጥሬ ገንዘብና ሌሎች ንብረቶች ያሏቸው ሰዎች ሳይቀር ማንም ሌላ ተቃዋሚ በሌለበት በማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች እንዲሁ በቀላሉ በሚሰጥ የደሃነት ማስረጃ በመጠቀም እንደፈለጉ የክሱን መጠንና ክስ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን በመወሰን በነጻ ክሶችን እያቀረቡ በርካቶችን ሲያጉላሉ እንደነበር በስፋት የሚታወቅ ነው፡፡ የደንቡ ረቂቅ ለውይይት በቀረበበት ወቅት በሁሉም ወገን በአጽንኦት እና ተደጋግሞ የተነሳውም በዚህ ረገድ ያለው መዛነፍና ብልሹ አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም ደንብ ቁጥር 17/2017 ከያዛቸው ቁልፍ መርሆዎች ውስጥ በቅድሚያ ተጠቃሹ “ማንኛውም የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጠው አቤቱታ የሚያቀርብ ወይም ያቀረበ ሰው የዳኝነት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት” የሚለው ነው፡፡ ይህ መርህ በአግባቡ ሥራ ላይ ሊውል ይገባል፡፡ ከፍ ሲል ደንቡን ማውጣት ለምን አስፈለገ በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር የተጠቀሱ ምክንያቶች በአግባቡ ምላሽ ሊያገኙ የሚችሉትን ይህን ገዥ መርህ በተግባር በማዋል ነው፡፡ ያለዚያ ግን ከዚህ በፊት እንደታዬው በቀጣይም በቂ የክስ ምክንያት ሳይኖር ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ በሆኑ ሌሎች አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች በቀላሉ ሊቋጩ የሚችሉ ጉዳዮች እንዲሁም ሌላ ሰውን በከርክር ለማድከም፣ ለማልፋትና ጉዳት እንዲደርስበት ለማድረግ የሚያስችሉ ክሶች ሁሉ ሊቀርቡና ጉዳትን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ሰዎችም በሥራ እና ሌሎች ጠቃሚነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ጊዜያቸውን ከማሳለፍ ወጥተው በእልህና አሸንፋለሁ በሚል እልክ ለረጅም ጊዜ በክርክር እንዲቆዩ በር ሊከፍት ይችላል፡፡ ሕግ አውጭውም ከገንዘብ መጠን አንጻርና ከጉዳዮች ምንነት ተነስቶ በፍርድ ቤቶች መካከል እርከን ለይቶ ያስቀመጠው የሥረ-ነገር ዳኝነት እንዲሁ የዳኝነት አገልግሎት ገንዘብ በማይከፍሉ ሰዎች ዘፈቀዳዊ ውሳኔና የተሰላ አቀራረብ ትርጉም አልባ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ሆነ በሌሎች ሀገሮች እንደሚደረገው ሁሉ የዳኝነት አገልግሎት ለመጠየቅ ፍርድ ቤት ፊት የሚቀርብ ሰው በአቀረበው አቤቱታ አንጻር ተገቢውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ (court fee) እና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ተጓዳኝ ወጭዎችን (other charges related to judicial service) መክፈል አለባቸው የሚለው መርሕ መከበርና በተግባር መዋል ያለበት ነው፡፡

### 4.3. ከዳኝነት ክፍያ ነጻ ስለሆኑ ሰዎችና የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይከፈልባቸው ክሶች

“ማንኛውም የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጠው አቤቱታ የሚያቀርብ ወይም ያቀረበ ሰው የዳኝነት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት” የሚለው መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም አቅም የሌላቸው ሰዎችን በተመለከተ ደግሞ የተለዬ ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡[17] ፍትሕ የማግኘት መብት ፍትኃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ቁልፍ አላባና የማንኛውም ሰው ሰብአዊ መብት ነው፡፡ ይህ በፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 እና አማራ ክልልን ጨምሮ በሌሎች ክልሎች ሕገ-

[17] As AI generates “While court fees are a common feature of many legal systems, they can pose a significant obstacle to access to justice, particularly for those with limited financial resources.”

መንግሥታት እንዲሁም ኢትዮጵያ ተቀብላ በአጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ውስጥ ዕውቅና ተሰጥቶት የሚገኝ መብት ነው፡፡ ይህ መብት የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም አቅም በሌላቸው ሰዎች ላይ እንቅፋት በዚህ ሕግ ምክንያት ፍትሕ የማግኘት መብታቸው እንዳይገደብ ወይም እንዳይገፈፍ በግልጽ አቋም ተይዟል፡፡ በፍርድ ቤት ፊት ፍትሕ የማግኘት መብትን በተሟላ ሁኔታ ማስጠበቅ የሚያስችሉ ሁለት ጉዳዮች በአንቀጽ 6 እና 7 ሥር በግልጽ ተመልክተዋል፡፡ እነርሱም፡-

○ ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ነጻ የሆኑ ሰዎች፣
○ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይከፈልባቸው ክሶች ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ከተከራካሪ ማንነት እና ከገንዘብ አቅም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህም ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ነጻ የሆኑ ሰዎች በሚል ተጠቅሷል፡፡ አንቀጽ 6 ከዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ነጻ የሆኑ ሰዎችን ይዘረዝራል፡፡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) "በሌላ ሕግ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሰዎች የዳኝነት ክፍያ ከመክፈል ነጻ ናቸው" በማለት የሚከተሉትን በግልጽ ከ(ሀ)- (ሐ) ጠቅሷል፡፡ ይኸውም፡-

- በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ደሃ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሰው፤
- ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር አካላት፤
- በወንጀል ክስ የዋስ መብቱን ለማረጋገጥ፣ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል ልዩ ልዩ አቤቱታ የሚያቀርብ ተከሳሽ፣ ለተጠረጠረ ወይም ለተከሰሰ ሰው ዋስ ለመሆን ወይም ዋስትና ለማስያዝ አቤቱታ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው

የዳኝነት ክፍያ ከመጠየቅ ነጻ ናቸው ሲል ደንግጓል፡፡

በአንቀጽ 6 (1) (ሀ) ሥር "በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ደሃ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ሰው" የዳኝነት ክፍያ ከመክፈል ነጻ ተብሎ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በደሃ ደንብ በነጻ ከመከራከር አንጻር አንቀጽ 6 (2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ደሃ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያቀረበ ሰው በተከራካሪ ወገን ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ የዳኝነት ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል ገንዘብ ወይም ሀብት እንዳለው መቃወሚያ የቀረበበትና ይኸው የተረጋገጠበት ሰው የዳኝነት ክፍያ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል" በማለት ከዚህ ቀደም በተግባር ይታዩ የነበሩ ክፍተቶችንና ብልሹ አሰራሮችን ለማስወገድ ይሞክራል፡፡ አንድ ሰው በፍርድ ቤት ፊት ፍትሕ እንዲሰጠው ሲያመለክት ለዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚሆን ገንዘብ ወይም ንብረት ያለው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ መረጋገጥ ያለበትም ከዚህ በፊት የወጣው የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ (1958) ከቁጥር 467-479 በሚደነግገው አግባብ ነው፡፡

ደንቡ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የደሃነት ማስረጃ ለመስጠት በአዋጅ ሥልጣን የተሰጣቸው የክልሉ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ናቸው በሚል በደንቡ ላይ ጥያቄ ሲያነሱ ይታያሉ፡፡ ለጥያቄያቸው መነሻ የሚያደርጉትም የተሻሻለው የማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 246/2009 ዓ.ም አንቀጽ 19 (3) "...ማስረጃ ለሚያስፈልጋቸውና በመንግሥት ለሚሰጡ አንዳንድ ነፃ አገልግሎቶች አመልካች ድሀ ስለመሆኑ የሚያውቁ ከሁለት ያላነሱ የቀበሌው ነዋሪ ምስክሮችን በመስማት ማስረጃዎችን ይሰጣሉ" በማለት የሚደነግገውን ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ደንቡ ሲረቀቅ እና በረቂቁ ላይ ውይይት ሲደረግና ግብአት ሲሰበሰብ ሁሉ ትኩረት የተሰጠውና ግልጽ ውይይት የተደረገበት ነጥብ ነው፡፡ ከተጠቀሰው ድንጋጌ ንባብ መገንዘብ እንደሚቻለው በፍርድ ቤት ለሚደረግ ክርክር የዳኝነት አገልግሎት ለመክፈል የገንዘብ አቅም የሌለው ስለመሆኑ የሚል ወይም ሌላ አቻ ቃልን አልያዘም፡፡ በመንግሥት የሚሰጥ ነፃ አገልግሎት ሲባል ከሕክምና አገልግሎት ጀምሮ በርካታ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ሊሸፍን የሚችል እንደሆነ

ከድንጋጌው ለመረዳት የሚቻል ቢሆንም በፍርድ ቤት ፊት ክስ ለማቅረብና ዳኝነት ለመጠየቅ ስለመሆኑ ግን ፍንጭ ሰጭ ነገር አልያዘም፡፡ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሳይከፍሉ በፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት ለማግኘት የራሱ ሥርዓት ያለውና ክርክር የሚደረግበት እንጅ እንዲሁ በአንድ ወገን ጠያቂነት (ሌላ ተቃራኒ ተከራካሪ ሳይጠራ) ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ምስክር በማሰማት በሚሰጥ ማስረጃ የሚወሰን አይደለም፡፡ የማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች አዋጅ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከዚህ ጋር በተያያዘ ሲሠራበት የቆየው ድንጋጌውን ከአውዱ ውጭ ለጥጦ በመተግበርና የሕግ አውጭውን ሀሳብ ባላገናዘበ መንገድ ይመስላል፡፡ ከዚህ ቀደም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በዚህ የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍሉ በነጻ የመከራከር ጉዳይ ላይ ግልጽ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ለምሣሌ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በቤተልሄም ፋርማሲቲዩካል ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጉዳይ (የሰ/መ/ቁ. 79555 ታህሳስ 02 ቀን 2005 ዓ.ም የተሰጠ ፍርድ) ላይ በግልጽ እንዳሰፈረው "... ክሱን የሚያቀርበው ወገን ድሀ በመሆኑ ምክንያት የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱን አቅርቦ እንዲያሰማ ሊፈቅድለት ይገባል? የሚለው ጉዳይ ሊለይ የሚችልበት ዝርዝር አፈፃፀም ደንቡም <u>ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467 እና ተከታዩ ድንጋጌዎች</u> ተመልክቷል" ብሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በወ/ሮ ሰሚራ ጀማል እና አቶ ናስር ሐጎስ (የሰ/መ/ቁ 188406) በነበረው ጉዳይ መስከረም 27 ቀን 2013 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ ላይ፡-

> <u>በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጋችን ከቁጥር 467 እስከ 479 ስር በተደነገገው መሠረት</u> ገንዘብ የሌለውና ለማግኘት የማይችል ማንኛውም ደሃ ሰው <u>ለሚያቀርበው ክስ የሚያስፈልገውን የዳኝነት ገንዘብ በሙሉም ሆነ በከፊል ለመክፈል የማይችል መሆኑን ገልጾ አቤቱታውን ካቀረበና ይህንኑ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት በማስረጃ ካስረዳ</u> በሙሉ ወይም በከፊል ዳኝነት ሳይከፍል የክስ መዝገቡ እንዲከፈትለትና በነጻ እንዲከራከር ሊፈቀድለት እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡

በማለት የወሰነ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡ አንድ ሰው በፍርድ ቤት ለአቀረበው አቤቱታ በወቅቱ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል የገንዘብ አቅም የለኝም ካለ በትክክልም በፍርድ ቤቱ የተገለጸለትን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመክፈል አቅም ያለው ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ በዚያው ወቅት ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት ታይቶ የሚወሰን እንጅ በሌላ ሰዓት በሌላ አካል ያለተቃራኒ ወገን አስተያዬት/መልስ እንዲሁ የሚረጋገጥ አይደለም፡፡ የዳኝነት አገልግሎት የሚከፈለው መጠን ሆነ በወቅቱ ደሃ ነኝ ያለው ሰው የገንዘብ አቅም ሁኔታ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ እንደሚደነግገው የጠያቂው አቤቱታ ከዋናው የክስ አቤቱታ ጋር ለተቃራኒ ወገን ደርሶት[18] በተቃራኒ ወገን ክርክር ሊቀርብበት የሚችልና በዚያው ጉዳዩ በቀረበለት ፍርድ ቤት መዝገብ ላይ ብይን ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ቀደም ባሉት የአጼ ኃይለሥላሴ እና የደርግ ዘመነ መንግሥትም ሲሠራበት የነበረ ትክክለኛ አካሄድ ነው፡፡ የፌደራሉ ፍርድ ቤቶችም የሚሰሩት በዚሁ አግባብ እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶችም ይህን ቀደም ሲል ሲሠሩበት የነበረውን ትክክለኛ አካሄድ እንዲተገብሩና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ ትርጉምን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በደንቡ ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ይህ ደንብ በክልሉ ምክር ቤት የወጣው በመጀመሪያ በእናት አዋጁ ማለትም በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ ቁጥር 297/2017 አንቀጽ 12 በተመለከተው አግባብ ስለሆነ ከላይ ከተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 246/2009 አንቀጽ 19 (3) አንጻር የሕጎችን ተዋረድ መሠረት አድርጎ የሚቀርብ የተለጠጠ ክርክር ቢኖር እንኳ በአሁኑ ሰዓት ይህ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም የአዋጅ ቁጥር 246/2009 19 (3) በፍርድ ቤት ፊት በነጻ አቤቱታ አቅርቦ መከራከር ስለመቻል በቀጥታ የሚለው ነገር ካለመኖሩ በላይ ይህ የቆዬ ሕግ ነው፡፡ ከእርሱ ይልቅ በቅርብ ጊዜ የወጣው አዋጅ 297/2017 በግልጽ በፍርድ ቤቶች ለሚደረግ ክርክር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ የደነገገ

[18] የደንቡ አንቀጽ 6 (3) "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)(ሀ) የተጠቀሰው ድንጋጌ ቢኖርም ደሃ ስለመሆኑ አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው ማመልከቻውን ከዋናው ክስ ወይም ጉዳይ ጋር አያይዞ ያቀርባል" ሲል ይደነግጋል፡፡

በመሆኑ ከጊዜ አንጻር (the recent law in time shall prevail over the older law) ሆነ ልዩ ሕግ ከመሆን (special law prevails over general law) አንጻር ተፈጻሚነት የሚኖረው ይህ አዋጅ ቁጥር 297/2017 አንቀጽ 12 እና ይህን ተከትሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 17/2017 ስለመሆኑ ምንም የማያጠራጥር ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚኖርን ጥርጣሬ ከላይ ከተገለጹት የፌዴራል ሰበር ሰሚ አስገዳጅ ትርጉም እና ከአዋጅ ቁጥር 297/2017 አንቀጽ 12 እንዲሁም ልዩ ሕግ ከሆነው ደንብ ቁ 17/2017 አንጻር አስወግዶ ወደትክክለኛው አሠራር መግባትና ደንቡን በወጣበት አግባብ በሥራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በደሃ ደንብ የተከራከረ ሰው በአሸነፈ ጊዜ ወይም ሀብት ሲያፈራ የዳኝነት ክፍያ መክፈል ያለበት ስለመሆኑ በደንቡ አንቀጽ 22 ሥር ተደንግጓል፡፡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) “በደሃ ደንብ መሠረት አቤቱታ አቅርቦ በክርክሩ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል አሸናፊ የሆነ ሰው በመጨረሻ ላይ ዳኝነት በጠየቀበት ክስ ልክ የዳኝነት ክፍያ እና የአገልግሎት ወጭን እንዲከፍል ይደረጋል” ሲል ይደነግጋል፡፡ ክሱን በሚያቀርብበት ወቅት የገንዘብ አቅም ያልነበረው ሰው ፍትሕ የማግኘት መብቱ ተከብሮ በነጻ ተከራክሮ ከአሸነፈ በአገኘው የዳኝነት አገልግሎት ተጠቃሚ ነውና በመጨረሻ ላይ በፍርዱ ከሚያገኘው ወይም ደግሞ በኋላ ንብረት ሲያፈራ አስቀድሞ ክሱን ሲያቀርብ መክፈል ይጠበቅበት የነበረውን የዳኝነት አገልግሎት ክፈል መባሉ ብዙም የሚያከራክር ጉዳይ አይመስልም፡፡ የሚከፍለው መጠን የሚሰላውም በክስ ወቅት ዳኝነት በጠየቀበት ክስ ልክ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሥ/ሥ/ሕጉ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ 22(4) እንደተመለከተው ረች ከሆነ ምናልባት የተለዬ ነገር ከሌለ በቀር ዞሮ ዞሮ ይህ የሚከፍለው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በተረቸው የሚተካ እንደሆነም መታወቅ አለበት፡፡ ደንቡ ከዚህም አልፎ ይህ በደሃ ደንብ የተከራከረው ሰው ተረች በሆነበት ጉዳይም በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ እንደተመለከተው ሀብት ሲያፈራ የዳኝነት ክፍያ እና የአገልግሎት ወጭን እንዲከፍል ይደረጋል ሲል በአንቀጽ 22 (4) ደንግጓል፡፡ያልተሰበሰበ የዳኝነት ክፍያ እና የአገልግሎት ወጭን በተመለከተ የዳኝነት አገልግሎቱ በተሰጠበት ፍርድ ቤት ትይዩ የሚገኘው ዓቃቤ ሕግ ወይም የሚመለከተው የዐቃቤ ሕግ የሥራ ክፍል ተከታትሎ ገቢ እንዲያደርግ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ወደሌላ ጉዳይ ከመሸጋገራችን በፊት ደንቡ የክርክር መራዘምን ለመቀነስ ሲባል ያካተተውን አዲስ ሥርዓት ከዚህ ላይ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ዋናውን ክስ ተቀብሎ ያስተናገደው ፍርድ ቤት የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል የገንዘብ አቅም እንደሌለው አረጋግጦ ብይን ከሰጠ በመርሕ ደረጃ ይህ ማረጋገጫ እስከ ይግባኝና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ለሚደረግ ክርክርም እንዲያገለግል በአንቀጽ 6 (4) ሥር “የተለዬ መቃወሚያ ካልቀረበ በስተቀር በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘ የድህነት ማስረጃ በበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት ይኖረዋል” ተብሎ ተደንግጓል፡፡

ሌላው ከተከራካሪ ማንነት ጋር በተያያዘ የዳኝነት አገልግሎት ከመክፈል ነጻ የሆነ ተከራካሪ በሚል እንደአዲስ በዚህ ደንብ የተካተተ “ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር አካላት” የሚለው ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የብዙ ሀገሮች ልምድ የሚያሳየው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚውለው ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከርና ለመደገፍ ነው፡፡ በአማራ ክልል ግን ፍርድ ቤቶች እንዲህ ዓይነት ገቢዎችን እንዲሰበስቡና ለራሳቸው ማጠናከሪያ እንዲያውሉ አልተፈቀደም፡፡ ወደፊት በዚህ ላይ የተለየ ውሳኔ በሕግ አውጭው እስኪሰጥ ድረስ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያም እንደየታክስ/የግብር ገንዘብ ወደ ክልሉ መንግሥት ገቢ የሚደረግና ምናልባትም በተዘዋዋሪ መንገድ ለፍርድ ቤት በበጀት መልክ ሊመጣ የሚችል ነው፡፡ እንዲህ በሆነበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር አካላት በከሳሽነት ወይም በሌላ ዘንግ (በተከሳሽ-ከሳሽነት፣ በፍርድ ተቃዋሚነት፣...) የዳኝነት አገልግሎት እንዲሰጣቸው አቤቱታ ሲያቀርቡ የዳኝነት እንዲከፍሉ መጠየቅ የመንግሥትን ገንዘብ በአንድ ኪስ አውጥቶ በሌላኛው የመንግሥት ኪስ የማስገባት ያህል ስለሚሆን ፋይዳ ቢስ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳ የመንግሥት የአስተዳደር

ተቋምን የሚወክሉ አላግባብ ሊሠሩ የሚችሉ ሰዎች ባይጠፉም በአጠቃላይ አነጋገር ግን እንዲህ ዓይነት የመንግሥት ተቋማት እንደግለሰቦች ሌላውን ተከራካሪ ለመጉዳት፣ ክርክር ለማጓተት፣ ... ወዘተ በማሰብ ወደክርክር ይገባሉ ወይም ደግሞ በትንሹም በትልቁም ነገር እንዲሁም ከፍርድ ቤት ውጭ በሌላ አማራጭ የአለመግባባት መፍቻ መንገድ ሊቋጩ የሚችሉ ጉዳዮችን ሁሉ ይዘው ወደፍርቤት ይቀርባሉ ተብሎ አይገመቱም፡፡ ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ የመንግሥት አስተዳደር አካላት (የክልሉ) ተከራካሪ በሆኑባቸው ጉዳዮች የዳኝነት አገልግሎት እንዲከፍሉ አይጠየቁም፡፡ ይህ በሌሎች ብዙ ሀገሮችም የሚደረግ አሠራር ነው፡፡[19]

የክልሉ መንግሥት የተለያዩ የልማት ድርጅቶች እና በከፊል በመንግሥት በጀት የሚደገፉ ልዩ ልዩ የሕግ ሰውነት የተሰጣቸው ተቋማት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ግን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን መረዳትና ደንቡን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህን ከማለፋችን በፊት ግን አንድ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም ሙሉ በሙሉ በፌዴራል መንግሥት አካላት በጀት የሚተዳደሩ የአስተዳደር አካላት ወይም የሌላ ክልል የአስተዳደር አካላት ተከራካሪ ቢሆኑ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ጉዳይ እንዴት ይታያል? የሚለው ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ በፌዴራል መንግሥት አካላት በጀት የሚተዳደሩ የአስተዳደር አካላት ወይም የሌላ ክልል የአስተዳደር አካላት ተከራካሪ ቢሆኑ ጉዳዩ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር ስለሚወድቅ ጉዳዩ ለአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አይቀርብምና ጥያቄው አይመጣም፡፡ ምናልባት ግን በውክልና ሥልጣን በአማራ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ቢሆን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ጉዳይ የሚታዬው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ሕግ መሠረት ስለሚሆን በዚያ አግባብ መሠረት መፈጸም ይገባል፡፡ በደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን ላይ እንደተገለጸው ለእንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ የአማራ ክልል ደንብ ቁ 17/2017 ተፈጻሚነት የለውም፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት መወሰኛ ደንብ ቁ 1/2017 ሙሉ በሙሉ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መንግሥት አስተዳደር አካላትን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ነጻ አያደርግም፡፡ የዚህ ደንብ አንቀጽ 21 የዳኝነት አገልግሎት የማይጠየቁትን (በነጻ እንዲከራከሩ የተፈቀደላቸውን) ሲዘረዝር በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩትን ያላካተተ በመሆኑ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ከሚከፍሉት ወገን እንደሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

በአንጻሩ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ ቁጥር 8/2016 የተከተለው የአማራ ክልል እና የፌደራሉ መንግሥት ከተከተለው የሚለይ ነው፡፡ የደንብ ቁ 8/2016 አንቀጽ 23 (6)፣(7) እና (8) ከሚደነግጉት መረዳት እንደሚቻለው "በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀርብ ጉዳይ"፣ "በመንግሥት የልማት ድርጅት የሚቀርብ ጉዳይ" እንዲሁም "በሕግ እውቅና ባላቸው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሚቀርብ ጉዳይ" የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ አይጠየቅበትም፡፡

ሌላውና በአንቀጽ 6 (1) (ሐ) የተመለከተው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ከመክፈል ነጻ የሆነው "በወንጀል ክስ የዋስ መብቱን ለማረጋገጥ፣ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል ልዩ ልዩ አቤቱታ የሚያቀርብ ተከሳሽ፣ ለተጠረጠረ ወይም ለተከሰሰ ሰው ዋስ ለመሆን ወይም ዋስትና ለማስያዝ አቤቱታ የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው" ነው፡፡ በወንጀል ጉዳይ ክርክር ሂደት በአንድ በኩል ያለው ተከራካሪ መንግሥት (ማለትም ፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ ወይም ማረሚያ ቤት) ስለሆነ በአንቀጽ 6 (1) (ለ) መሠረት የዳኝነት አገልግሎት ከመክፈል ነጻ ነው፡፡ በሌላ ወገን ያለው ደግሞ ተጠርጣሪ፣ተከሳሽ ወይም ፍርደኛ ሲሆን ይህም የዋስ መብቱን ለማረጋገጥ፣ የቀረበበትን የወንጀል ክስ ለመከላከል ልዩ ልዩ አቤቱታ ቢያቀርብ የዳኝነት አገልግሎት

[19] ለምሣሌ ከላይ በግርጌ ማስተዋሻ 11 ስር ከተጠቀሱት bRadyshevska Olesya R የተጻፈውን ይመልከቱ፡፡

ከመክፈል ነጻ ነው፡፡ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ለተጠርጣሪ ወይም ለተከሳሽ ዋስ ለመሆን ወይም ዋስትና ለማስያዝ አቤቱታ የሚያቀርብ ማንኛውም 3ኛ ወገን የሆነ ሰውም የዳኝነት አገልግሎት ከመክፈል ነጻ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቆመው ደንቡ ከአካተታቸው አዳዲስ ቁም-ነገሮች መካከል በአንቀጽ 7 ሥር የተመለከተውና የደሃነት ማስረጃ ማቅረብን የማይጠይቀው "የዳኝነት ክፍያ ስለማይከፈልባቸው ክሶች" የሚለው ይገኝበታል፡፡ ከተለያዩ መነሻ ምክንያቶች፣ ፖሊሲዎች እና የሕግ ማዕቀፎች በመነሳት አንዳንድ ክሶች በፍርድ ቤቶች ፊት ሲቀርቡ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይጠየቅባቸው ናቸው፡፡ በተለይም በተለያዩ የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎች ለሕዝብ ጠቀሜታ እንዳላቸው ታምኖ ድጋፍ የሚደረግላቸው፣ ከተጋላጭነትና ከተጠቂነት አንጻር ልዩ ጥበቃና ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩና በፍርድ ቤት ፊት ፍትሕ የማግኘት መብትን ለማስፋትና ለማበረታታት ሲባል ጉዳያቸውን ያለምንም ክፍያ እንዲያቀርቡ ማድረግ በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ተቀባይነት ያገኘ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በአዲሱ የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት መወሰኛ ደንብ አንቀጽ 7 መሠረት የሚከተሉት ክሶች የዳኝነት ክፍያ አይጠየቅባቸውም፡፡ እነርሱም

- በሕፃን ሞግዚት የሚቀርብ የወላጅነት ይታወቅልኝ ወይም የልጅ አስተዳደግን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ፤
- በቤተሰብ ሕግ መሠረት በማንኛውም ሰው የሚቀርብ የቀለብ ይወሰንልኝ አቤቱታ፤
- የቤት ውስጥ ሠራተኛ ከቀጣሪና ተቀጣሪ ግንኙነት በመነጨ በአሠሪ ላይ የሚቀርብ የደመወዝ ክፍያ አቤቱታ፤
- ማንኛውም ሠራተኛ ወይም የሠራተኞች ማኅበር የሚያቀርበው የሥራ ክርክር፤
- ከውል ውጭ በሚደርስ የሞት ወይም የአካል ጉዳት ጋር በተያያዘ በተጎጅ ወይም በተጎጅ ጥገኞች የሚቀርብ በቀለብ መልክ የሚከፈል ካሣ አቤቱታ፤
- አካልን ነጻ ለማውጣት እንዲሁም በግዳጅ ስወራ የሚገኝን ሰው በተመለከተ የሚቀርብ አቤቱታ፤
- በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች፣ በአረጋዊያን እና ሌሎች ልዩ ድጋፍን በሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጉዳይ ላይ የሚቀርብ የወል የሰብአዊ መብቶች የማስከበር አቤቱታ፤
- በግብረ-ሥጋ ነጻነት እና ንጽሕና እንዲሁም ለተፈጥሮ ባሕሪ ተቃራኒ የሆነ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ጥቃት ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም የፍትሐ ብሔር አቤቱታ፤
- የአካባቢ ጥበቃንና ደኅንነትን እንዲሁም የወል መጠቀሚያን በተመለከተ በመብት ተቆርቋሪ ወይም ሞጋች አካላት ወይም በሕጋዊ ተወካዮች የሚቀርብ አቤቱታ፤
- አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት አንድ ሠራተኛ በግሉ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስለት ለሚያቀርበው አቤቱታ

ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው እነዚህ ክሶች ለምን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዳይጠየቅባቸው እንደተወሰነ ለመረዳት አዳጋች ባለመሆኑ በእያንዳንዳቸው ላይ ዝርዝር ማብራሪያ ማቅረብ አላስፈለገም፡፡

ስናጠቃልለውም በአዲሱ ደንብ መሠረት በአንቀጽ 6 ሥር የተጠቀሱት ሰዎች እና በአንቀጽ 7 ሥር የተዘረዘሩ የክስ አይነቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የማይከፍሉና የማይጠየቅባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በደንቡ አንቀጽ 13 (1) ከ(ሀ)- (ረ) የተመለከቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚከፈሉ የዳኝነት ክፍያዎች እነዚህን ሰዎችና የክስ አይነቶች አይመለከቱም፡፡ አንቀጽ 13 (2) በግልጽ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ክፍያዎች ከዳኝነት ክፍያ ነጻ የተደረጉ ሰዎች እና ክሶች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም" ሲል የደነገገ መሆኑን መመልከትና ከዚህ አንጻር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 4.4. የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ስለሚከፈልበት ጊዜ እና የአከፋፈል ሥርዓት

ደንብ ቁጥር 17/2017 በአንቀጽ 8 ሥር የዳኝነት ክፍያን ስለማስከፈል፣ስለሚከፈልበት ጊዜ እና ስለአከፋፈል ሥርዓቱ ይደነግጋል፡፡ በዚህም መሠረት የዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) በየደረጃው የሚገኝ ሬጅስትራር ወይም ሌላ አግባብነት ያለው የፍርድ ቤት ሠራተኛ የዳኝነት ክፍያ የማስከፈል ኃላፊነት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በንዑስ (6) ሥር ደግሞ "በየደረጃው የሚገኝ የፍርድ ቤት ሬጅስትራር ወይም ሌላ አግባብነት ያለው የፍርድ ቤት ሠራተኛ የዳኝነት ክፍያን ሲያስከፍል ክስ የቀረበበት ጉዳይ በገንዘብ ሊተመን የሚችል መሆን ወይም በገንዘብ ሊተመን የማይችል መሆኑን እና ከዚህ አንጻር ሊከፈል ስለሚገባው ትክክለኛ የዳኝነት ክፍያ መጠን በጥንቃቄ በመለየት ክፍያው እንዲፈጸም ለሚመለከተው ሠራተኛ ወዲያውኑ ማስተላለፍ" እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ከዚህም አልፎ መዝገብ ተከፍቶ የቀረበለት ወይም በቀጥታ ለችሎት አቤቱታ የቀረበለት የፍርድ ቤት ዳኛ በደንቡ መሠረት መከፈል የሚገባው የዳኝነት ክፍያ በትክክል መከፈሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንደአለበት በንዑስ (8) ሥር ተደንግጓል። በንዑስ (9) ሥር ደግሞ መዝገብ ከተከፈተ በኋላ በተቃራኒ ወገን ከሚቀርብ መቃወሚያ በመነሣት የሚከፈል የዳኝነት ክፍያ ወይም ተጨማሪ የዳኝነት ክፍያ በሚኖርበት ጊዜ ሬጅስትራሩ ወይም አግባብነት ያለው ሌላ ሠራተኛ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ብይን ወይም ትዕዛዝ መሠረት ተገቢው የዳኝነት ክፍያ እንዲከፈል መደረግ እንዳለበት በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የፍርድ ቤት ሬጅስትራሮች፣ ሌሎች በዚህ ሥራ ላይ የተመደቡ የፍርድ ቤቱ ሠራተኞች እንዲሁም ጉዳዩ የሚቀርብላቸው ችሎት ዳኞች ኃላፊነታቸውን በውል ተገንዝበው ተገቢው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዲፈጸም ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ኃላፊነት በአግባቡና በንጽሕና አለመወጣት እንደሁኔታው በሥልጣን አላግባብ መገልገል ወይም ደግሞ በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ባለመወጣት ሊያስጠይቅ የሚችል እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ይህ አንቀጽ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበትን ጊዜ እና የአከፋፈል ሥርዓትም ይደነግጋል፡፡ይኸውም አንቀቀጽ 8 (3) እንደሚደነግገው "የዳኝነት ክፍያ የሚፈጸመው የፍርድ ቤት መዝገብ ከመከፈቱና ቁጥር ከመሰጠቱ በፊት ወይም እንደሁኔታው አቤቱታው በሌላ ተከራካሪ ወገን በተከፈተ መዝገብ ከመያያዙ ወይም ደግሞ ለችሎት ከመቅረቡ በፊት ነው፡፡" ይህ እንዳለ ሆኖ በከሳሽ ዘንግ ወደ ክርክር እንዲገባ የተፈቀደለት ወይም በተሰጠ ፍርድ ሙብቴ ተነክቷል ወይም በክርክሩ ተካፋይ መሆን ይገባኝ ነበር በማለት የመቃወሚያ አቤቱታ የሚያቀርብ ሰው በቀረበ ጊዜ ደግሞ በተከፈተው መዝገብ ላይ ተገቢውን የዳኝነት ክፍያ እንዲከፍል ተደርጎ ወደክርክሩ እንደሚገባ በንዑስ (4) ላይ ተመልክቷል፡፡

የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሥርዓቱን በተመለከተም አንቀጽ 8 (2) መከፈል የሚገባው የዳኝነት ክፍያ "ፍርድ ቤቱ አመቺ ነው ብሎ በመረጠው በጥሬ ገንዘብ፣ በባንክ በኩል፣ በክሬዲት እና በዴቢት ካርድ ወይም በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴ" ሊፈጸም እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በተጨማሪም ባለጉዳዮች በኤሌክትሮኒክ በሚደረግ የአቤቱታ አቀራረብ (ኢ-ፋይሊንግ) ወይም በማንኛውም የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ ዘዴ በመጠቀም አቤቱታ ማቅረብ በሚችሉበት ወቅት ክፍያውን በክሬዲት ካርድ፣ በዴቢት ካርድ፣ በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ወይም አመቺ በሆኑ ሌሎች የክፍያ ዘዴዎች አማካይነት መፈጸም እንደሚችሉ በንዑስ (5) ላይ ተመልክቷል፡፡

## 4.5. በገንዘብ ሊተመኑ የሚችሉ ክሶች እና በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠንና የሥሌት ዘዴ

የደንቡ አንቀጽ 9(1) እንደሚደነግገው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ፡-

- በጉዳዩ ዓይነት፣
- ጉዳዩ በገንዘብ የሚተመን ወይም የማይተመን እንደመሆኑ እንዲሁም
- አቤቱታውን ተቀብሎ እንደሚያስተናግደው የፍርድ ቤት እርከን

መጠኑ እና ስሌቱ እየተለየ የሚፈጸም ነው፡፡

በጉዳይ ዓይነት፣ በገንዘብ የማይተመኑ እና ጉዳዩ እንደሚቀርብበት ፍርድ ቤት እየታዬ የሚወሰነው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በደንቡ ውስጥ በቁርጥ የተመለከተ ስለሆነ ለአፈጻጸም ያን ያህል የሚያስቸግር አይደለም፤ዝርዝር ማብራሪያ ማቅረብንም የሚጠይቅ አይመስልም፡፡ እነዚህ፡-

- በአንቀጽ 11 (በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ ክሶች)፣
- አንቀጽ 13 (ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈሉ የዳኝነት ክፍያዎችና መጠን)፣
- አንቀጽ 14 (ለክለሳ ወይም በይግባኝ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ)፣
- አንቀጽ 15 (በክርክር ሂደት ወይም ከውሳኔ በኋላ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች የሚከፈል የዳኝነት ክፍያ)፣
- አንቀጽ 17 (ፍርድ ለማስፈፀም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ)
- አንቀጽ 19 (ለይግባኝ ክርክር ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ) እና
- አንቀጽ 20 (በሰበር ለሚታይ ጉዳይ ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ)

በሚል አርዕስት ስር የጉዳዩን ዓይነቶች፣ አቤቱታዎቹ የሚቀርቡበትን ፍርድ ቤት፣ በየትኛው የክርክር ደረጃ ላይ እንደቀረቡ፣ እንዲሁም በቀጥታ ክስ፣ በይግባኝ፣በአፈጻጸም እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መቅረባቸውን መሠረት በማድረግ ለዋናው የክርክሩ ጉዳይ ወይም ለአፈጻጸሙ የሚከፈለውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እና ከዋናው ክርክር በተጓዳኝ ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና በፍርድ ቤቶች ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን በቁርጥ ደንግገዋል፡፡ ለምሣሌ ያህል መጥቀስ ቢያስፈልግ  በአንቀጽ 11 እንደተደነገገው በገንዘብ ሊተመኑ የማይችሉ የተለያዩ አቤቱታዎች ለፍርድ ቤት ሲቀርቡ አቤቱታው የቀረበው፡

- ለወረዳ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር)፣
- ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር)፣
- ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ከሆነ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)

እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት በአንድ ዳኛ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ ከወረዳ ፍርድ ቤቶች በተሻለ ልምድና ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ በሚታሰብ ሦሥት ዳኛ እንዲሁም በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤት በሆነው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በልምድ፣በትምህርት ደረጃ እና በመሳሰሉት ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሻሉ ናቸው ተብሎ በሚታሰብ ሦሥት ዳኞች የሚታይና የእነዚህን ያህል ዳኞች ጊዜና ጉልበት ተጠቅሞ ለሚሰጥ አገልግሎት ከዚህ በላይ የተመለከቱ የዳኝነት ክፍያ መጠኖች ተገቢ ናቸው ተብሎ የታሰበ ገንዘብ በቁርጥ ተመልክቷል፡፡ ይህ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች[20] እና በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች[21] የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንቦች ከተመለከተው ጋር አንድና ተመሳሳይ ነው፡፡

ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚከፈሉ የዳኝነት ክፍያዎችና መጠን ደግሞ አንቀጽ 13 (1) ከ (ሀ)-(ረ) በሚደነግገው መሠረት

- ለተከራካሪ ወገን ወይም ለምስክር መጥሪያ ለማውጣት ለእያንዳንዱ ምስክር ብር 50 (አምሳ ብር)፣
- የፍርድ ወይም በመዝገብ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም የሰነድ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግልባጭ ለመውሰድ በገጽ ብር 5 (አምስት ብር)፣

[20] አንቀጽ 8 (1)፣(2) እና (3)፡፡
[21] አንቀጽ 16 (1)፣(2) እና (3)፡፡

- በቤተሰብ ሕግ መሠረት በባልና ሚስት መካከል ንብረትን አስመልክቶ የሚደረግን ስምምነት ወይም ውል በፍርድ ቤት ለማረጋገጥ ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር)፣
- በፍርድ ቤት ጊዜአዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም የእግድ ትዕዛዝ እንዲሰጥ፤የግልግል ዳኝነት በፍርድ ቤት አማካይነት እንዲሾም፣ በግልግል ዳኝነት የተሰጠ ጊዜያዊ የመጠባበቂያ ዕርምጃ ወይም ሌላ ትዕዛዝ ተፈጻሚ እንዲሆን ለሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)፣
- የግልግል ዳኛ በሰጠው ትዕዛዝ ላይ እና ሌሎች ከፍርድ ቤት ባለሙያ፣ ከውርስ አጣሪ ወይም ከሌሎች ባለሙያዎች የፍርድ ቤቱን የማህተም ማረጋገጫ አገልግሎት ለማግኘት ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 100 (አንድ መቶ ብር)፣
- ጊዜው ያለፈበት የይግባኝ ወይም የሰበር ማስፈቀጃ አቤቱታ ለማቀርብ ብር 100 (አንድ መቶ ብር)

ይከፈላል፡፡ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ውጪ ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት አገልግሎት ከተጠየቀ እንደሁኔታው ሬጅስትራሩ ወይም ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት አገልግሎቶች ጋር ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ በሚሆነው ርዕስ ሥር የተመለከተው ክፍያ እንዲከፈል እንደሚያደርግም በንዑስ (3) ሥር ተደንግጓል፡፡ እነዚህ ሁሉ በአብዛኛው በፌዴራሉና በኦሮሚያ ካለው ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ላይ የተመለከተው የክፍያ መጠን ጉዳዮቹ ከያዙት ጥቅም/ሙብት፣ በክርክር ሂደት ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት ከሚጠይቁት ጊዜና ጉልበት፣ … ወዘተ የሚታዩና የሚመዘኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ክፍያዎች ከዳኝነት ክፍያ ነጻ የተደረጉ ሰዎች (ለምሣሌ በደሃ ደንብ የሚከራከርን) እና ክሶች ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆኑ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ (2) ላይ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ፍትሕ የማግኘት ሙብትን የሚያሰናክሉ ወይም የሚገድቡ አለመሆናቸው በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት መካከል አንዳንዶቹ ቀደም ሲል በነበረው ሕግም የነበሩና የክፍያ መጠናቸው እንደጨምር የተደረጉ ናቸው፡፡ለምሳሌ ለምስክር ወይም ለተከራካሪ ወገን የሚሰጥ መጥሪያ 0.50 ሣንቲም ያስከፍል የነበረው አሁን 50 ብር ሆኗል፡፡ በእውነት ለመናገር ከብር የመግዛት አቅም አንጻር ሲታይ የተደረገው ጭማሪ ለስሙ ያህል ነው፡፡ በአጼ ኃይለሥላሴ ወይም በደርግ ዘመነ መንግሥታት እና በኢህአዴግ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ የነበረው የወቅቱ የ0.50 ሣንቲም የመግዛት አቅም እና በአሁኑ ሰዓት ያለው የ50 ብር የመግዛት አቅም ያን ያህል የተራራቀ ሆኖ አይታይም፡፡ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታም ቢሆን ብር 90 ይከፈልበት የነበረው አሁን በአዲሱ ደንብ 10 ብር ብቻ ጨምሮ ብር 100 የሚከፈልበት ነው፡፡ ይህ ስሙ ጭማሪ ተባለ እንጅ ከብር የመግዛት አቅም አንጻር ከታየ ጭማሪ ሳይሆን ቅነሳ የተደረገበት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡

ሌሎች በርካቶች ደግሞ በቀድሞው ሕግ ያልነበሩና አሁን በአዲሱ ደንብ የተካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህ የክፍያ ምክንያቶች የሚያስከፍሉት የገንዘብ መጠን ከያዙት ጥቅም አንጻርና ፍርድ ቤት ከሚሰጠው አገልግሎት አንጻር ሲታይ በዛ ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ከዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ነጥብ በደሃ ደንብ እንዲከራከሩ የተፈቀደላቸው ሰዎችን ጨምሮ ሌሎች ከዳኝነት አገልግሎት ክፍ ነጻ የሆኑ ሰዎች እና የዳኝነት አገልግሎት በማይከፈልባቸው በርካታ የክስ ዓይነቶች ላይ እነዚህ አሁን በአንቀጽ 13 (1) ሥር የተዘረዘሩት የክፍያ ምክንያቶች ሆነ የተመለከቱት የክፍያ መጠኖች ተፈጻሚነት የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡

ለክለሳ ወይም በይግባኝ ለሚቀርቡ ጉዳዮች ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ እንደዚሁ አንቀጽ 14 (1) እስከ (3) ባሉት ድንጋጌዎቹ የይግባኝ አቤቱታ ለወረዳ፣ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሲቀርቡ በቁርጥ እንደቅድም ተከተሉ ብር 1,000፣2,000 እና 3,000 ሊከፈል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ ከፌዴራሉና ከኦሮሚያ ጋር ተመሳሳይ

ነው፡፡ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ እንዲከለስ አቤቱታ ለወረዳ፣ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሲቀርቡ አሁንም እንደቅደም ተከተል ብር 1,500፣2,000 እና 2,500 ሊከፈል እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ ከለሳን አስመልክቶ ኦሮሚያ በዝምታ ያለፈውና ምናልባትም እንደይግባኙ የሚያስከፍል የሚችል ሲሆን የፌዴራሉ ግን በአማራ ክልል ከተመለከተው ያንሳል፡፡ በአማራ ክልል በቅርብ ጊዜ የጸደቀውን የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ/ም ተከትሎ በበቂ ምክንያት ሆነ ያለበቂ ምክንያት ሊቀርቡ የሚችሉ የክለሳ አቤቱታዎች ፍርድ ቤቶችን የሚያጥለቀልቁ እንዳይሆን (ከአንዳንድ መነሻ ምክንያቶች በመነሳት በሚወሰድ ግምት- ለምሣሌ የተከራካሪነት ልማድ፣የመሳሰሉት) ከፍ ያሉ ሥጋቶች አሉ፡፤ ይሁንና በዚህ ላይም የግለሰቦች በአስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳይገደብ በአንቀጽ 7 (10) ሥር ደሃ መሆንን ማረጋገጥ ሳያስፈልግ “አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት አንድ ሠራተኛ በግሉ በአስተዳደር አካል የተሰጠው ውሳኔ በፍርድ ቤት እንዲከለስለት ለሚያቀርበው አቤቱታ” የዳኝነት ክፍያ እንደማይጠየቅበት በግልጽ ተደንግጓል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጥንቃቄዎች የተደረጉ መሆኑን ሳያገናዝቡ አንዳንዶች እንዲሁ ሾላ በድፍን በክልሉ ውስጥ ደሃ በሚሉት የኅብረተሰብ ክፍል ሽፋን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የተጋነነ ነው በማለት የሚያቀርቡት ትችት ውሃ የማይቋጥርና ከጀርባው ሌላ ሕገ-ወጥ ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡

በክርክር ሂደት ወይም ከውሳኔ በኋላ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች የሚከፈል የዳኝነት ክፍያን አስመልክቶ እንደዚሁ አንቀጽ 15 ከንዑስ (1) እስከ (5) ድረስ የአቤቱታውን ዓይነትና የሚያስከፍለውን መጠን ይደነግጋል፡፡ ይኸውም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ፍርድ፣ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ወይም በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት በቀረበ አቤቱታ ለሚሰጥ አገልግሎት፡-

- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ውሳኔ አስነሥቶ ወደ ክርክሩ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ ብር 500 (አምስት መቶ)፣
- ፍርድን ለመቃወም ለሚቀርብ አቤቱታ መቃወሚያውን ያቀረበው ወገን አስቀድሞ ተከፍሎ በነበረው ክፍያ ልክ፣
- ፍርድ እንደገና እንዲታይ ለሚቀርብ አቤቱታ አቤቱታውን ያቀረበው ወገን አስቀድሞ የተከፈለውን ክፍያ፣
- በክርክር ሂደት ጣልቃ ለመግባት ለሚቀርብ አቤቱታ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ አመልካቹ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር)፣ እና
- ተከሳሽ የሆነ ወገን ሦሥኛ ወገን በክሱ ውስጥ እንዲገባ አቤቱታ ሲያቀርብ ተከሳሹ ሦሥኛው ወገን ኃላፊነት አለበት በሚለው የገንዘብ መጠን ልክ፤

ሊከፍል እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ ይህ ሁሉ የፌደራሉ እና የኦሮሚያ ደንቦች ከሚደነግጉት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ከዚህ ሌላም አንቀጽ 16 ከተከራካሪ ወገኖች አንዳቸዉ በክርክር ሂደት ውስጥ የአቤቱታ ማሻሻል ጥያቄን ጨምሮ በሚያቀርቡት ማመልከቻ ምክንያት የክርክር ሂደቱ ወደኋላ የሚመለስ ከሆነ ፍርድ ቤቱ እንደ ነገሩ ሁኔታ አስቀድሞ ተደረጎ የነበረው የክርክር ሂደት የደረሰበትን ደረጃ፣ የፍርድ ቤቱን ጊዜ እና ወጪ ከግምት ውስጥ በማስገባት አቤቱታ አቅራቢው ተመጣጣኝ የዳኝነት ክፍያ እንዲከፈል ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል ደንግጓል።

ፍርድ ለማስፈፀም ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ የሚደነግገው አንቀጽ 17 ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ፍርድ ለማስፈፀም ለሚቀርብ የአፈፃፀም አቤቱታ፡-

- እስከ ብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 300 (ሶስት መቶ ብር)፣
- ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 500 (አምስት መቶ ብር)፣

- ከብር 200,001 (ሁለት መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ከሆነ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር),
- ከብር 500,001 (አምስት መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ 1,000,000,000 (አንድ ሚሊዮን ብር) ከሆነ ብር 1,500 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር)፣
- ከብር 1,000,001 (አንድ ሚሊዮን አንድ ብር እስከ ብር 10,000,000 (አሥር ሚሊዮን ብር) ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር)፣ እንዲሁም
- ከብር 10,000,001 (አሥር ሚሊዮን አንድ ብር) በላይ ከሆነ ብር 3,000 (ሶስት ሺህ ብር)

እንደሚያስከፍል ደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በፍርድ አፈጻጸም ወቅት የተያዘ ወይም የተከበረ ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል አቤቱታ ሲቀርብ አቤቱታ አቅራቢው ፍርዱ ሊፈጸምብኝ አይገባም የሚለው ንብረት ወይም ገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) እና የፍርድ አፈጻጸሙ በገንዘብ ሊተመን የማይችል ጉዳይን የተመለከተ የአፈጻጸም አቤቱታ ከሆነ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ሊከፈል እንደሚገባ በአንቀጽ 17 (2) እና (3) እንደቅደምተከተሉ የተደነገገ መሆኑን ማዬት ይቻላል፡፡ ይህ ሁሉ ከፌዴራሉ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ የኦሮሚያም ቢሆን እስከ 10,000 ባለው የገንዘብ መጠን አፈጻጸም ላይ ባሉት ክፍልፋዮች ካልሆነ በስተቀር ተመሳሳይ ነው፡፡

አንቀጽ 19 ለይግባኝ ክርክር ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ የሚደነግገውን ስንመለከት፡-

- የሥር ፍርድ ቤት በመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ላይ ተመሥርቶ ወደ ዋናው ጉዳይ ሳይገባ መዝገቡን የዘጋው ከሆነ በዚህ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲያቀርብ የክርክሩ የገንዘብ መጠን ከግምት ሳይገባ ብር 500 (አምስት መቶ ብር)፣
- የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲቀርብ በሥር ፍርድ ቤት የተከፈለው ገንዘብ ግማሹን ይግባኝ ባዩ፣
- የሥር ፍርድ ቤት ዳኝነት ከተጠየቀበት ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ከፊሉን ወይም የተወሰነውን ባለመቀበል በከፊሉ ላይ ውሳኔ ከሰጠና ይህንኑ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ከቀረበ ይግባኝ ባዩ ሳይወሰንልኝ ቀርቷል በሚለው ላይ ብቻ ከዚህ ከፍ ብሎ በተመለከተው መሠረት ተሰልቶ፣
- የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ረቺ የሆነ ወገን ውሳኔው የሥነ-ሥርዓት ጉድለት አለበት ወይም በትክክለኛው ጭብጥ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ አይደለም በማለት መስቀለኛ ይግባኝ ወይም መስቀለኛ መቃወሚያ የሚያቀርብ ወገን ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር)፣
- መስቀለኛ ይግባኙ ወይም መስቀለኛ መቃወሚያው የቀረበው በከፊል ውድቅ የተደረገን የውሳኔ ክፍል ከሆነ የዳኝነት ክፍያው ከዚህ በላይ ከመጀመሪያው ቀጥሎ በተከታታይ በተጠቀሱት 2ኛ እና 3ኛ ላይ የተጠቀሱት አንጻር ተሰልቶ

ሊከፈል እንደሚገባ ከንዑስ (1) እስከ ንዑስ (5) ደንግጓል፡፡

በመጨረሻም በሰበር ለሚታይ ጉዳይ ስለሚከፈል የዳኝነት ክፍያ የሚደነግገው አንቀጽ 20 ከንዑስ (1)- (4) ባሉት ድንጋጌዎቹ፡-

- የሰበር አቤቱታው የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታው የቀረበው የከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ሩብ (1/4ኛ)፣

- የሰበር አቤቱታ የቀረበው በገንዘብ በሚተመን ጉዳይ ሆኖ አቤቱታውም የቀረበው የጠቅላይ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ከሆነ ለዚህ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ሩብ (1/4ኛ)፤
- ጊዜአዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከዋናው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊባልበት በሚችል ትዕዛዝ ላይ ተመሥርቶ ከይግባኝ በኋላ የሰበር አቤቱታ ሲቀርብ ለይግባኝ ሰሚው የመጨረሻ ፍርድ ቤት የተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ግማሹ፣ እና
- በአስተዳደር አካል የአስተዳደር ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ለሰበር ችሎት በቀጥታ በሚቀርብበት ጊዜ ብር 3,000 (ሶስት ሺህ ብር) ይከፈላል በማለት አመላክቷል፡፡

በቁርጥ ከተመለከቱት ውጭ ያለው የዳኝነት ክፍያ መጠን ስሌት ለብዙ ሰዎች አደናጋሪ እንደሆነ በየዞኖች ከቀረቡ ጥያቄዎች መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ሊከፈል የሚገባው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ የሚሰላው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ በግልጽ ሊመለስ ይገባዋል፡፡ ይህን ለመመለስም የደንቡ አንቀጽ9 (2) የሚደነግገውን እንደሚከተለው እንፈትሻለን፡፡ በቅድሚያ በድንጋጌው ሥር የተመለከተውን እንዳለ በማስፈር ለማፍታታት እንሞክር፡፡ አንቀጽ9 (2) ቀጥሎ ያለውን ይደነግጋል፡-

> በቁርጥ ከተመለከቱት ውጭ ያለው የዳኝነት ክፍያ መጠን ስሌት በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው የዳኝነት ክፍያ ተመን ሠንጠረዥ እንደተመለከተው በመቶኛ ተሰልቶ የሚፈጸም ሲሆን ይህም የቀረበው የክስ አርዕስት እና/ወይም ዳኝነት እንዲሰጥበት የተጠየቀው ጉዳይ የያዘው መጠን የሚወድቅበትን እርከን በመለዬት ቀድሞ ያለውን እርከን ጣራ በመቀነስ ለእርከኑ በተቀመጠው መቶኛ በማባዛትና ቀደም ብሎ ያለውን እርከን የክፍያ መጠን ጣሪያ በመደመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

የዚህን ድንጋጌ ቅልፍ አላባዎች ለመለየት ስንሞክር የምናገኘው፡-

ሀ) በቅድሚያ “የቀረበው የክስ አርዕስት” እና/ወይም “ዳኝነት እንዲሰጥበት የተጠየቀው ጉዳይ የያዘው መጠን” ስንት እንደሆነ መለዬት ይገባል፤ ይህን መጠን “ፐ” እንበለው፡፡

ለ) በመቀጠል ይህ ስንት እንደሆነ የተለየው “የቀረበው የክስ አርዕስት” እና/ወይም “ዳኝነት እንዲሰጥበት የተጠየቀው ጉዳይ የያዘው መጠን” (ፐ) የሚወድቅበትን እርከን ከደንቡ ጋር አባሪ ሆኖ ከተያያዘው ሠንጠረዥ አንጻር በማስተያየት የትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ መለዬት ያስፈልጋል፤

ሐ) ከዚያም ከተለየው እርከን ቀድሞ [(ፐ) ከሚወድቅበት እርከን አስቀድሞ] ያለውን እርከን ጣራ መውሰድ ያስፈልጋል (ይህን “ጨ” እንበለው)፤ ለዚህ እርከን ጣራ የተመለከተውን በመቶኛ የተሰላውን የዳኝነት ክፍያ መጠንም መያዝ ይጠይቃል፡፡ ይህን የዳኝነት ክፍያ መጠን “ጀ” ብለን እንያዘው፡፡

መ) ከዚህ በመቀጠል ስንት እንደሆነ የተለየው ማለትም የቀረበው የክስ አርዕስት እና/ወይም ዳኝነት እንዲሰጥበት የተጠየቀው ገንዘብ (“ፐ”) በሠንጠረዡ ላይ ከ”ፐ” በፊት ያለውን ጣሪያ ገንዘብ (“ጨ” ) መቀነስና የሚገኘውን ቀሪ ሂሳብ በሠንጠረዡ “ፐ” ፊት ለፊት በተመለከተው የመቶኛ ስሌት ማባዛት ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚገኘውን የዳኝነት ክፍያ መጠን “ደ” ልንለው እንችላለን፡፡

በመጨረሻም “ጀ” ን እና “ደ”ን በመደመር የምናገኘው ሂሳብ “የቀረበው የክስ አርዕስት” እና/ወይም “ዳኝነት እንዲሰጥበት የተጠየቀው ጉዳይ ለዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መዋል ያለበትን የገንዘብ መጠን ያሳየናል፡፡ ለምሣሌ አንድ ከሳሽ ግምቱ 12 ሚሊዮን በሚሆን የንብረት ግምት መሠረት በተከሳሽ ላይ ክስ አቀረበ እንበል፡፡ ይህ ሰው መክፈል ያለበት የዳኝነት ገንዘብ ስንት ነው? ይህ 12 ሚሊየን የንብረት ግምት በሠንጠረዡ ላይ ከ10,000,001 – 20,000,000 በሚለው እርከን ላይ

ይወድቃል፡፡ ከዚህ እርከን በፊት ባለው እርከን ላይ የተመለከተው ጣሪያ የገንዘብ መጠን 10,000,000 የሚል ነው፡፡ በዚህ ፊት ለፊት የተመለከተው የዳኝነት አገልግሎት ሂሳብ 330,000 ነው፡፡ ይህ የሚያዝ የሂሳብ ስሌት ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከ12,000,000-10,000,000 = 2,000,000 ይቀራል፡፡ ይህን 2,000,000 ገንዘብ 12 ሚሊዮን (ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን) በሚወድቅበት የመቶኛ ማባዣ ማለትም በ2.9% ስናባዛ የምናገኘው ውጤት 2,000,000 x 2.9% = 58,000 ይሆናል፡፡ ይህን አስቀድሞ ከያዝነው 330,000 ጋር መደመር አለብን፡፡ ይህም ማለት 330,000+58,000=388,000 ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ለ12 ሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ ክስ ጉዳይ የዳኝነት አገልግሎት የሚከፈለው መጠን ብር 388,000 ይሆናል፡፡

በሌላ አገላለጽ በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ የሚከፈለውን የዳኝነት ክፍያ መጠን ለማወቅ በቅድሚያ ክስ የቀረበበት/ዳኝነት የተጠየቀበት መጠን የሚወድቅበትን እርከን ሠንጠረዡ ላይ ሂዶ ማዬትና ከዚህ እርከን አስቀድሞ ያለውን ጣሪያ ፊት ለፊት የተመለከተውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ገንዘብ መጠን መያዝ ነው፡፡ ከዚያም ክስ ከቀረበበት/ዳኝነት ከተጠየቀበት መጠን ላይ በሠንጠረዡ አስቀድሞ ባለው እርከን ላይ ያለውን ጣሪያ ተቀናሽ ማድረግ ነው፡፡ ስንቀንስ የምናገኘውን መጠንም በሠንጠረዡ ላይ ክስ የቀረበበት/ዳኝነት የተጠየቀበት መጠን የሚወድቅበትን እርከን ማባዣ በመጠቀም እናሰላለን፡፡ በዚህ የመቶኛ ስሌት የምናገኘውን ገንዘብና አስቀድሞ ክስ የቀረበበት/ዳኝነት የተጠየቀበት መጠን የሚወድቅበትን እርከን በፊት ላይ የተመለከተውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን እንደምርበታለን፡፡ የሁለቱ ድምር ክስ የቀረበበት/ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ የሚያስከፍለውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ይሰጠናል፡፡ ይህ ደግሞ ለእያንዳንዱ ጉዳይ በተመሳሳይ የሚፈጸም ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች አንቀጽ 9 (2) ሠንጠረዡን በማጣቀስ ስለመቀነስ፣ ቀሪውን በመቶኛ ስለማባዛት እና እንደገና አስቀድሞ ባለው እርከን ላይ የተመለከተውን ስሌት ስለመደመር የሚደነግገውን ትተው በቀጥታ በሠንጠረዡ ላይ የተመለከተው መጠን የዳኝነት አገልግሎት ሂሳብ ነው ተብሎ እንደሚወሰድ የሚገልጹት የተሳሳተ ነው፡፡ በዚህ ላይ እንደምሣሌ የሚወስዱትንና ስሌቱ ችግር እንዳለበት የሚገልጹትን እንመልከት፡፡ ይኸውም የብር 39,000 እና የብር 40,000 የክስ መጠን ያላቸው የሁለት ክስ አቅራቢዎችን ይወስዱና የብር 40,000ን በቀጥታ ከሠንጠረዡ በማዬት በ9% ስሌት ብር 3,600 ይከፍላል ይላሉ፡፡ የብር 39,000ን ግን ከዚህ በፊት ባለው እርከን ላይ የተመለከተውን በ10% ስሌት እስከ 20,000 ላለው ብር 2,000 ይይዙና ቀሪውን 19,000 የክሱ መጠን በሚገኝበት እርከን አንጻር በሚገኘው የመቶኛ ስሌት (9%) አባዝተው ብር 1,710 ስለሚመጣ የሁለቱ ድምር 2,000+1,710=3,710 ነው በማለት የብር 40,000 ያስከፍላል ካሉት ብር 3,600 ጋር እንደሚጣረስ ያስረዳሉ፡፡ ይህ ግን ሁለቱንም ጉዳዮች አንቀጽ 9 (2) በሚደነግገው መሠረት በተመሳሳይ ካለማስተናገዳቸው ማለትም የብር 40,000ን ስለመቀነስ፣ማባዛትና መደመር የተደነገገውን በመተው በቀጥታ በሠንጠረዡ ፊት ለፊት የተመለከተውን ስሌት በመወስዳቸው ምክንያት የመጣ ነው፡፡ ትክክለኛው አሠራር ግን ልክ የብር 39,000 እንደተሰላው ሁሉ የብር 40,000ንም አንቀጽ 9 (2) በሚደነግገው መሠረት ማስላት ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ስሌቱን ስንሠራ በቅድሚያ ብር 40,000 የሚወድቅበት እርከን በፊት ያለውን ብር 2,000 እንይዛለን፡፡ ከዚያም ከ40,000 ላይ ከ40,000 በፊት ባለው እርከን ጣሪያ ላይ ያለውን 20,000 ስንቀንስ 20,000 ይቀራል፡፡ ይህን ቀሪ ሂሳብ 40,000 በሚወድቅበት እርከን ላይ በተመለከተው መቶኛ ማባዣ (9%) ስናባዛ 20,000 x 9% = 1,800 ይመጣል፡፡ አስቀድሞ ባለው እርከን የያዝነው 2,000+1,800= 3,800 ይመጣል፡፡ ስለሆነም የብር 40,000 ክስ የሚከፈልበት የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን ብር 3,800 እንጅ ብር 3,600 አለመሆኑን እንረዳለን፡፡ በዚህ መሠረት በሕጉ እንደተመለከተው ሁሉም በተመሳሳይ ሲስተናገድ የሚፈጠር ተቃርኖ አይኖርም፡፡ ይህ አይነት አሠራር የተወሰደውም ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ደንብ አንቀጽ 14 ነው፡፡

### 4.6. ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት

ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ወደከፋዩ ተመላሽ የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡ተመላሽ የሚደረገው መጠን ደግሞ አቤቱታው ወይም ክርክሩ እንደደረሰበት ደረጃ የሚለያይ ነው፡፡ የደንቡ አንቀጽ 21 የሚመለከተውም ለዳኝነት የተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታና ተመላሽ ስለሚደረገው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ እነዚህም ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ ንዑስ አንቀጽ (6) በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡ ድንጋጌው ለዳኝነት አገልግሎት የተከፈለ ገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው አግባብ ለከፋዩ ሊመለስ ይችላል ካለ በኋላ ዝርዝሩንና መጠኑን አስመልክቶ፡-

- ከሳሽ የሆነው ወገን የዳኝነት ክፍያውን ፈጽሞ መዝገቡ ቀጠሮ ከመያዙ በፊት ወይም ቀጠሮ እንደተሰጠው መጥሪያው ወጪ ከመሆኑ በፊት ክሱን ለማቋረጥ ቢወስን ለዳኝነት ከከፈለው ገንዘብ ላይ 5% (አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ይመለስለታል፤
- ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት መዝገቡን መርምሮ ከሳሹ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መነሻ ምክንያት የለውም ወይም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መዝገቡን ቢዘጋ ከተከፈለው ዳኝነት ላይ 10% (አሥር በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ለከሳሹ ይመለስለታል፤
- ከክስ መሰማት በፊት ክስ ቢቋረጥ ከተከፈለው ዳኝነት 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፤
- ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ከክስ መሰማት በፊት በስምምነት ወይም በእርቅ ቢጨርሱ ከተከፈለው ዳኝነት ላይ 10% (አሥር በመቶ) ተቀንሶ ለከሳሹ ይመለሳል፤ ተከሳሹም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቦ ከሆነ በዚሁ አግባብ ይፈጸማል፤
- ከሳሽ፣ የተከሳሽ ከሳሽ፣ ጣልቃ ገብ ወይም ተቃዋሚ ምስክር ከመሰማቱ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች ከመቅረባቸው ወይም ከመመርመራቸው በፊት አቤቱታውን ቢያነሣ ከተከፈለው የዳኝነት ክፍያ ውስጥ 20% (ሃያ በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፤
- በዳኛ አማካይነት ለፍርድ ቤት-መር አስማሚ ተመርቶ የነበረ ጉዳይ ጉዳዩ በአስማሚ በኩል እልባት ካገኘ ከሳሹ ወይም ይግባኝ ባዩ ለዳኝነት የከፈለው ገንዘብ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ተቀንሶ ቀሪው ተመላሽ ይደረጋል፤

በማለት ይደነግጋል፡፡

### 4.7. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ደንብ ቁ 17/2017 በሥራ ላይ ሲውል ቀድም ሲል በነበረው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ሕግ እና አሁን አዲስ በወጣው ደንብ አፈጻጸም ላይ መደናገር እንዳይኖር ለማድረግ የሚያስችል የመሸጋገሪያ ድንጋጌ በደንቡ ውስጥ ተካትቷል፡፡ በዚህም መሠረት የደንቡ አንቀጽ 25 (1) “ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነባሩ ደንብ መሠረት መስተናገዳቸው ይቀጥላል” ሲል ደንግጓል፡፡ ይህም ማለት ደንቡ ሥራ ላይ ከዋለበት ሚያዝያ 11 ቀን 2017 ዓ/ም በፊት የተከፈተና በየትኛውም እርከን ፍርድ ቤት ላይ የሚገኝ የክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ ጉዳይ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያው ሆነ ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎች የሚከፈሉት ቀድሞ ሲሠራበት በነበረው ሕግ ነው፡፡ ይህ ከወረዳ ላይ የነበረ ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ከከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ የነበረ ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የነበረም ወደ ክልሉ ሰበር ችሎት ሲቀርብ ሁሉ የሚስተናገደው በቀድሞው ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ መዝገብ ለማስከፈት ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ትዕዛዞችንና ብይኖችን ለማሰጠት ለሚቀርብ አቤቱታ እንዲሁም ከፍርድ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለሚቀርብ አቤቱታ ሁሉ ያገለግላል፡፡

ለተቃራኒ ተከራካሪ ወይም/እና ለምስክር መጥሪያ ለማውጣት ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከፈል ገንዘብ ቢኖር ተፈጻሚ የሚሆነው የቆየው ሕግ ነው፡፡

ሆኖም ይህ አጠቃላይ መርሕ የራሱ የሆኑ ልዩ ሁኔታዎች ወይም በስተቀሮች (exceptions) አሉት፡፡ ልዩ ሁኔታዎቹም በዚሁ አንቀጽ 25 (2) ሥር በግልጽ ተመልክተዋል፡፡ ይኸውም፡-

ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ ከወጣ በኋላ፡-

ሀ. በበላይ ፍርድ ቤት ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ መሠረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ በሚያየው በቀድሞው ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ፍርድ ቤት እንደገና እንዲታይ በሚል እንደአዲስ ሙሉ ክርክር እንዲደረግ ተብሎ የተመለሰ ከሆነ፤

ለ. ጭብጥ ተለይቶ ማስረጃ ከመሰማቱ ወይም ከመመርመሩ በፊት ተዘግቶ የቆዬ መዝገብ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ጥያቄ የቀረበ ከሆነ፤

ሐ. በይግባኝ ወይም በሰበር ፍርድ ክርክር ሂደት የቆዩትን ሳይጨምር ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ ከሁለት ዓመት በፊት የተሰጠ ትዕዛዝን፣ ብይንን፣ ፍርድን ወይም ውሳኔን ለማስፈጸም የቀረበ የአፈጻጸም አቤቱታ ከሆነ፤

በዚህ ደንብ መሠረት የተመለከተው የዳኝነት ክፍያ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

በማለት ተደንግጓል፡፡

በ(ሀ) ሥር የተደነገገው አዲሱ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተከፈተና በክርክር ላይ የነበረ ጉዳይ አሁን ይህ አዲስ ደንብ ከወጣና ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በበላይ ፍርድ ቤት ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ መሠረት እንደገና እንዲታይ ተብሎ እንደአዲስ ቀድሞ በተመለከተው ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ፍርድ ቤት ፊት ሙሉ ክርክር የሚደረግበት ከሆነ ማናቸውም የዳኝነት አገልግሎት ክፍያና ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎች የሚፈጸሙት በነባሩ ሕግ መሠረት ሳይሆን በዚህ በአዲሱ ደንብ መሠረት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ጉዳዩ አስቀድሞ ቢጀመርም ሙሉ ክርክሩ እንደገና እንዲደረግ ብይን፣ትዕዛዝ፣ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ ተፈጻሚ የሚሆነው ይህ አዲሱ ደንብ ነው፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ልዩ ልዩ ትዕዛዞችንና ብይኖችን ለማሰጠት ለሚቀርብ አቤቱታ (ለምሳሌ እግድ ለማሰጠት ወይም ለማስነሳት)፣ለተቃራኒ ተከራካሪ ወይም/እና ለምስክር መጥሪያ ለማውጣት ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚከፈለው ገንዘብ እንዲሁም ከፍርድ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ ቢኖር የሚስተናገደው በአዲሱ ደንብ መሠረት ነው፡፡ ይህ ወደቀድሞ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ችሎት ተመላሽ የተደረገና እንደገና ሙሉ ክርክር የተደረገበት ጉዳይ በሂደት በመዝገቡ ላይ ብይን፣ትዕዛዝ፣ፍርድ ወይም ውሳኔ ቢሰጥና በዚህ ላይ እንደገና የይግባኝና የሰበር ክርክር የሚቀጥል ቢሆንም ለዳኝነት አገልግሎትና ተያያዥ ሌሎች ክፍያዎች ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ አዲሱ ደንብ ነው፡፡ የዚህ ሁሉ ዋና ምክንያቱ መዝገቡ ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ቢከፈትም በተጨባጭ ግን ሙሉ ክርክሩና ቀጣይ የይግባኝና የሰበር የክርክር ሂደቶች እንደገና እንዲታዩ (re-trial de novo) በመደረጉና አዲሱ ደንብ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የተከፈተ መዝገብ ከሚጠይቀው ጉልበትና ጊዜ እምብዛም ስለማይለይ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 25 (2)(ለ) ሥር ሌላ የአንቀጽ 25 (1) ልዩ ሁኔታ (በስተቀር) ተደንግጓል፡፡ ምንም እንኳ መዝገቡ ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተከፈተ ቢሆንም "ጭብጥ ተለይቶ ማስረጃ ከመሰማቱ ወይም ከመመርመሩ በፊት ተዘግቶ የቆዬ መዝገብ" ከሆነ ይህ መዝገባ እንደገና እንዲንቀሳቀስ ጥያቄ ከቀረበ ከዳኝነት ክፍያና ተያያዥ አገልግሎቶች ጋር የሚጠየቀው ክፍያ የሚስተናገደው በአዲሱ ደንብ መሠረት ነው፡፡ በክርክር ሂደት ብዙ ጊዜና ጉልበት የሚወስደው ጭብጥ ከተለዬ በኋላ የሚከተለው ማስረጃ መስማት እና መዝገቡን መርምሮ ፍርድ መስጠት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተግባራት ከመከናወናቸው በፊት ተዘግቶ የቆየ መዝገብ ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ እንደገና

እንዲንቀሳቀስ ከተደረገና ማስረጃ ማስማቱ የሚቀጥል ወይም/እና መዝገቡን መርምሮ የመሥራት ሥራ የሚቀጥል ከሆነ ጉዳዩ የሚስተናገደው በአዲሱ ደንብ መሠረት ነው፡፡

በመጨረሻም ይህ ደንብ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተከፈተ ነገር ግን ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ ከሁለት ዓመት በፊት የተሰጠ ትዕዛዝን፣ ብይንን፣ ፍርድን ወይም ውሳኔን ለማስፈጸም አቤቱታ የሚቀርብ ከሆነም ተፈጻሚ የሚሆነው አዲሱ ደንብ ነው፡፡ ይህም ማለት በጉዳዩ ላይ ትዕዛዝ፣ ብይን፣ፍርድ ወይም ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ወደኋላ ሲቆጠር ከሁለት አመት በላይ ከሆነና አዲሱ ደንብ ወደ ሥራ ከተገባ በኋላ ያን ከተሰጠ ከሁለት አመት በላይ የሆነውን ትዕዛዝ፣ ብይን፣ፍርድ ወይም ውሳኔ ለማስፈጸም አቤቱታ ከቀረበ ተፈጻሚ የሚሆነው አዲሱ ደንብ ነው፡፡ ለምሣሌ በ2012 ዓ/ም የተሠጠ ፍርድን ለማስፈጸም የሚቀርብ የአፈጻጸም አቤቱታ ቢኖር ለአፈጻጸም ዳኝነት የሚከፈለው ሆነ ሌሎች ነገሮች ቢኖሩ ተፈጻሚ የሚሆነው አዲሱ ደንብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሚያዝያ 8 ቀን 2017 ዓ/ም (አዲሱ ደንብ ከሥራ ላይ ከመዋሉ ትንሽ ቀናት በፊት) የተሰጠ ብይንን፣ትዕዛዝን፣ፍርድን ወይም ውሳኔን ለማስፈጸም ሚያዝያ 9 ቀን 2019 ዓ/ም አቤቱታ ቢቀርብ (ብይኑ፣ትዕዛዙ፣ፍርዱ ወይም ውሳኔ ከተሰጠ ከሁለት አመት በላይ ቆይቶ) ተፈጻሚ የሚሆነው ይኸው አዲሱ ደንብ ነው፡፡

ነገር ግን ይህ በአንቀጽ 25 (2) (ሐ) ስር የተደነገገው የልዩነት ልዩነት/የበስተቀር በስተቀር (exception to an exception) አለው፡፡ ምንም እንኳ ይህ አዲስ ደንብ ከሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የቀረበ የአፈጻጸም አቤቱታ ቢኖርና ይህ አቤቱታ የሚመለከተው ከተሰጠ ከሁለት አመት በላይ የሆነን ትዕዛዝ፣ ብይን፣ፍርድ ወይም ውሳኔ ለማስፈጸም የቀረበ ቢሆንም ይህን ያህል ጊዜ የቆየው በይግባኝ ወይም በሰበር ፍርድ ክርክር ሂደት የተነሳ ከሆነ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያው ሆነ ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎች የሚሰሉት በአዲሱ ደንብ ሳይሆን በነባሩ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በ2012 ዓ/ም የተሠጠ ፍርድን ለማስፈጸም የቀረበ የአፈጻጸም አቤቱታ ቢኖርና ይህን ያህል ጊዜ ዘግይቶ የቀረበው በነበረው የይግባኝ ወይም እስከሰበር ሰሚ ችሎት (በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፊት ይሁን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት) የደረሰ ክርክር ምክንያት ከሆነ ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግ የቀድሞው እንጅ አዲሱ ደንብ አይሆንም፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ ለማሳየት እንደተሞከረው በአማራ ክልል ውስጥ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ሲሠራበት የነበረው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መወሰኛ ሕግ በርካታ ያልሸፈናቸው ጉዳዮች የነበሩበት ነው፡፡ ሕጉ ከወጣም ከ70 ዓመታት በላይ ሆኖታል፡፡ በዚህ አሮጌ ሕግ የተመለከተው የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ መጠን አሁን ካለው የብር የመግዛት አቅም አንጻር ሲታይ ኢምንት ነበር፡፡ ከዚህ ግባ ለማይባል የዳኝነት አገልግሎትና ሌሎች ተያያዥ ክፍያዎች የሚቆረጠው ደረሰኝ ለአገልግሎት ከሚከፈለው በላይ ዋጋ የሚያስወጣበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ክልሉ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል በተለዬ ክርክር የሚበዛበትና እስከመጨረሻ እርከን ድረስ ሰዎች በክርክር ጊዜያቸውን፣ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን የሚያባክኑበት እንደሆነ የፍርድ ቤት ዳታዎች ያሳያሉ፡፡ ከቅን ልቦና ውጭ ሁሉ ክርክር የሚደረግበት፣ ሌሎች የአለመግባባት መፍቻ መንገዶች እየተተው በትንሹም በትልቁም ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት የሚመጣበት ልምድ እየሰፋ የመጣበት ሁኔታ እንዳለ ታይቷል፡፡ በዚህ የተነሳም በየጊዜው የመዛግብት ክምችትና የፍርድ ቤቶች በጉዳይ ብዛት መጨናነቅ እንዳለ ማወቅ ተችሏል፡፡ ለዚህ ዓይነት ነባራዊ ሁኔታ አሰተዋጽኦ ከሚያደርጉት አንዱ የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ ለረጅም ዓመታት ሳይከለስ ወይም ሳይለወጥ መቀጠሉ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በዚህ ምክንያትም ይህ አዲሱ ደንብ ቁጥር 17/2017 እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ የደንቡ ዓላማዎችም በግልጽ የተመላከቱ ናቸው፡፡ በተለይ የክስ ምክንያት የሌላቸው፣ከፍርድ ቤት ውጭ ማለቅ የሚችሉ እንዲሁም ከቅን ልቦና ውጭ ወደ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮችን በመቆጣጠር ለዳኝነት ሥራ አካሄድ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻል የሚለው ዓላማ ጎልቶ የሚታይ

ነው፡፡ ከዚያ ውጭ እግረ-መንገድ የመንግሥትን ወጭ በተወሰነ መጠን መጋራት ያለ ቢሆንም ደንቡ ግን የመንግሥትን ገቢ ለማሳደግ በሚል እንዳልወጣ በእርግጠኛነት መናገር ይቻላል፡፡

አንዳንድ ሰዎች በተለይም ከጠበቆች መካከል የተወሰኑት ደንቡ የሰዎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ይጥሳል በማለትና ለደሃ ሰዎች የተቆረቆሩ በመምሰል ያለምንም ደጋፊ ማስረጃና ትንታኔ ትችት ሲያቀርቡ ይሰማል፡፡ ይህ ግን ደንቡን በሚገባ ካለማንበብ የሚመነጭ ወይም ደግሞ ከሌላ ስውር ፍላጎት የሚነሳ እንደሆነ ማሳዬት ይቻላል፡፡ ደሃ የሆነ ሰው ፍትሕ የማግኘት መብቱ እንዳይገደብ በነጻ መከራከርን የሚደግፍ ደንብ ነው፡፡ ሌሎች ጥቅሞቻቸውንና መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ ግድ የሚሆንባቸውና ሌላ አማራጭን ለመጠቀም የማይችሉ ወይም ቢጠቀሙ እንኳ አጥጋቢ መፍትሔን ማግኘት የሚቸገሩ ሰዎች እንደዚሁ በነጻ ክስ ሊያቀርቡ የሚችሉበትን በር የከፈተ ደንብ ነው፡፡ ብዙ የክስ ዓይነቶች የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ እንዳይጠየቅባቸው በግልጽ ድንጋገዎችን የያዘ ደንብ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ ያለውን ማኅበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በሚገባ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም አጠቃላይ እንደሀገር ሊኖር የሚገባውን ቀጣይ ትክክለኛ አሠራር ታሳቢ በማድረግ የወጣ ሕግ ነው፡፡ በብዙ ጉዳዮች ላይ የፌደራል መንግሥትን እና የኦሮሚያ ክልልን ተሞክሮ በመዳሰስና ከአማራ ክልል አውድ አንጻር በማጣጣም የወጣ ሕግ ነው፡፡ በመሆኑም ሕጉ በወጣበት አግባብ በተግባር እንዲውል ሁሉም የሚመለከታቸው ወገኖች በኃላፊነት መንፈስ ሊሠሩ ይገባል፡፡

======== ========      ==========      =========  ==========    =============     =========